# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

## የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# በፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ ለህብረት ስራ ማህበራት ድጋፍ ለመስጠት የተዘረጋውን የአሰራር ስርዓት በአግባቡ መፈፀሙንና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ የተከናወነ የክትትል ኦዲት ሪፖርት

ታህሳስ 2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ


ማውጫ ............................................................................................................i

ክፍል አንድ ............................................................................................................ 1

መግቢያ ............................................................................................................1

የክትትል ኦዲቱ ዓላማ ............................................................................................................2

የክትትል ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ............................................................................................................2

የክትትል ኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ............................................................................................................2

ክፍል ሁለት ............................................................................................................ 3

በክትትል ኦዲት ወቅት የተገኙ የኦዲት ግኝቶች፣ ............................................................................................................ 3

2.1 የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲና የክልል ኅብረት ስራ ማስፋፊያ ኤጀንሲዎች/ቢሮዎች/ ለህብረት ስራ ማህበራት የሚሰጡ ድጋፎችን ተግባራዊ ለማድረግ የክትትል፣ የቁጥጥርና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥርዓት መዘርጋታቸውን በተመለከተ፤ ............................................................................................................3

የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ በአገር አቀፍ ደረጃ የህብረት ስራ ፖሊሲ ቀርጾ አፈፃፀሙን መከታተሉን በተመለከተ፣ ............................................................................................................3

የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ ለህብረት ስራ ማህበራት የሚሰጠውን ድጋፍ በረጅምና በአጭር ጊዜ እቅድ ውስጥ ማካተቱን እና ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፣4

የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ ህብረት ስራ ማህበራት ከመደራጀታቸው በፊት እንዲሁም ከተደራጁ በኋላ እንዲያድጉ ጥናትና ምርምር ማድረጉን እና የክልል ማስፋፊያ አካላት ጥናት እንዲያደርጉ እገዛ ማድረጉን በተመለከተ፣ ............................................................................................................7

የህብረት ስራ ማህበራት በፌዴራል እና በክልል ስለመደራጀታቸው እንዲሁም የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ በአገር አቀፍ ደረጃ የህብረት ስራ ሊግ ማቋቋሙን በተመለከተ፤ ............................................................................................................10

ኤጀንሲው የሥልጠና ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ ............................................................................................................13

የህብረት ስራ ማህበራት ሂሳብ በየዓመቱ ኦዲት ስለመደረጉ፤ ............................................................................................................27

የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲና የክልል ማስፋፊያ አካላት ለተደራጁ ማህበራት የኢንስፔክሽን አገልግሎት መስጠታቸውን በተመለከተ፣ ............................................................................................................34

የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲና የክልል ማስፋፊያ አካላት ለባለድርሻ አካላት ግንዛቤ መፍጠራቸውን በተመለከተ፤ ........................................................................36

2.2 የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ በደንቡ መሠረት የተሰጠውን ኃላፊነት በብቃት እና ኢኮኖሚያዊ በሆነ ሁኔታ ለመወጣት ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራቱን እና ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት የዘረጋ መሆኑንና ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤ ........................................................................38

የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ ከማስፋፊያ አካላትና ከማህበራት ጋር የሚደረግ የመረጃ ልውውጥ እና አያያዝን ሥርዓትን በተመለከተ፣ ........................................45

ክፍል ሦስት ........................................................................ 49

የመደምደሚያ ሀሳብ (Conclusion)........................................................................ 49

3.1 እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው........................................49

ክፍል አራት........................................................................ 54

የማሻሻያ ሀሳቦች (Recommendation)........................................................................ 54

አባሪ 1 ፡አነስተኛ የሴቶች ተሳትፎ ያለባቸው ህብረት ስራ ማህበር ................................ 55

አባሪ 2፡ የአዋጭነት ጥናት የሌላቸው........................................................................ 56

አባሪ 3 ፡ደንብ እና መመሪዎች የሌላቸው ........................................................................ 61

አባሪ 4፡ ከ3 ዓመት በላይ ኦዲት ሳይደረጉ የቆዩ ሀ/ስ/ማህበራት .................................... 66

አባሪ 5፡ ኦዲት ተደርገው የማያውቁ ህብረት ስራ ማህበራት .......................................... 68

አባሪ 6 ፡የጽ/ቤት እና መስሪያ ቦታ የሌላቸው ........................................................................ 71

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. በሀገራችን የሕብረት ስራ ማህበራትን በዘመናዊ መልኩ ማደራጀት ከተጀመረ 57 ዓመታትን አስቆጥሯል፡፡ በመሆኑም የህብረት ስራ ማህበራት በአገራችን ፈጣን ፣ ቀጣይና ፍትሃዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማትና እድገት ከማረጋገጥና የአባላትን ብሎም የህዝብን ተጠቃሚነት ከማሳደግ አንፃር እና ድህነትን ለማስወገድ ማህበራቱ ዘርፈ ብዙ ስራዎችን ያከናውናሉ፡፡ በዚህም በከተማ እና በገጠር ለሚኖረው የህብረተሰብ ክፍል በርካታ ጠቀሜታዎች ይሰጣሉ፡- የአምራቹንና የሸማቹን ህብረተሰብ በምርትና አገልግሎት በማስተሳሰር ለተጠቃሚው ጥራት ያለውን ምርት በተመጣጣኝ ዋጋ በተፈለገ ጊዜና ቦታ ለማቅረብ የሚረዱ፣ የሸማቹን መብትና ፍላጎት የሚያስጠብቁ፣ አምራቹም ለሚያመርተው ምርት ተገቢውን ዋጋ እንዲያገኝ የሚያስችሉ ድርጅቶች ናቸው፡፡

2. የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ የህብረት ስራ ማህበራትን እንቅስቃሴ የማጎልበት፣ የሰው ኃይል የማሰልጠን፣ ጥናትና ምርምር የማካሄድ ተግባር በአዋጅ ቁጥር 985/2008 የተሰጠው የመንግስት መ/ቤት ነው፡፡

3. የሕብረት ስራ ማህበራት በተለያየ የአደረጃጀት እርከን ተደራጅተዋል፡፡ የመጀመሪያው እርከን መሰረታዊ የሕብረት ስራ ማህበር የሚባል ሲሆን የሕብረት ስራ ማህበራት ዓይነቶችን ያቀፈና ተመሳሳይ ፍላጎት ባላቸው ሰዎች የተቋቋመ ነው፡፡ ሁለተኛው የሕብረት ስራ ማህበራት አደረጃጀት እርከን የሕብረት ስራ ሕብረት /ዩኒዩን/ ሲሆን ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ተመሳሳይ አላማ እና ተግባር ያላቸው መሰረታዊ የሕብረት ስራ ማህበራት የሚያቋቁሙት የሕብረት ስራ ማህበር ነው፡፡ ሶስተኛው እርከን ፌዴሬሽን በመባል የሚታወቅ ሲሆን ሁለት ወይም ከሁለት በላይ በሆኑ ተመሳሳይ ዓላማና ተግባር ባላቸው ዩኒየኖች ይመሰረታል፡፡ አራተኛው እርከን ሊግ ሲሆን በአገር አቀፍ ደረጃ የሚመሰረት ነው፡፡

## የክትትል ኦዲቱ ዓላማ

4. የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ ለህብረት ስራ ማህበራት ድጋፍ ለመስጠት የዘረጋው የአሰራር ስርዓት በአግባቡ ተፈጻሚና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ ከ2001 እስከ 2003 በጀት ዓመት የተከናወነው የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ላይ የተጠቀሱ ኦዲት ግኝቶች እና የተሰጡ ማሻሻያ ሃሳቦች ላይ የተወሰደ የማስተካከያ እርምጃ መኖሩን እንዲሁም ተገቢውን የክትትል እና የቁጥጥር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ለማረጋገጥ ነው፡፡

## የክትትል ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

5. የክትትል ኦዲቱ በዋናኛነት በፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ እና በናሙና በተመረጡ 3 የክልል ህብረት ሥራ ኤጀንሲዎች (አዲስ አበባ፣ ኦሮሚያ እና አማራ)፣ በክልሎቹ ስር በሚገኙ 10 የወረዳ እና ክፍለ ከተማ/ዞን ህብረት ሥራ ማስፋፊያ አካላት እና ኤጀንሲዎች እንዲሁም 4 ዩኒየኖች እና 4 መሰረታዊ የህብረት ሥራ ማህበራት ሲሆን፤ የክትትል ኦዲቱ በ2004 ዓ.ም በተደረገው የክዋኔ ኦዲት መሰረት ከ2005 ዓ.ም እስከ 2009 ዓ.ም ድረስ የህብረት ስራ ማህበራትን ድጋፍ አሰጣጥ በተመለከተ በተሰጠው የማሻሻያ ሃሰብ እና ኤጀንሲው ባዘጋጀው የድርጊት መርሃ ግብር መሰረት የተደረጉ የማስተካከያ እርምጃዎች ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡

6. የክትትል ኦዲቱ የተከናወነው ከ2005 በኃላ ያሉትን የስትራቴጂክ እቅድ፣ አመታዊ የእቅድና አፈፃፀም ሪፖርቶች፣ የህብረት ስራ ማህበራት ላይ የተሰሩ የኦዲት እና ኢንስፔክሽን ሪፖርቶች ፣ የህብረት ስራ ማህበራትን በተመለከተ የወጣ አዲስ አዋጅ (985/2008)፣ አዋጁን ለማስፈፀም የሚወጡ ረቂቅ ደንብ እና ረቂቅ መመሪያ፣ ረቂቅ ህብረት ስራ ፖሊሲ እንዲሁም የተለያዩ የአተገባበር እና ስልጠና ማንዋሎች እና የመሳሰሉትን ማስረጃዎች በመከለስ ፣ በፅ/ቤቱ እና በመስክ የሚገኙ የሚመለከታቸውን የስራ ኃላፊዎችን ቃለ መጠይቅ በማቅረብ እንዲሁም በአካል ተገኝቶ የመስክ ምልከታ በማድረግ ተከናውኗል፡፡

## የክትትል ኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

7. የክትትል ኦዲቱን ለማከነወን እንደ መመዘኛ መስፈርት የተመረጡት በኦዲቱ ወቅት የነበሩ የኦዲት ግኝቶችና የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች ናቸው፡፡

# ክፍል ሁለት

## በክትትል ኦዲት ወቅት የተገኙ የኦዲት ግኝቶች፣

### 2.1 የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲና የክልል ኅብረት ስራ ማስፋፊያ ኤጀንሲዎች/ቢሮዎች/ ለህብረት ስራ ማህበራት የሚሰጡ ድጋፎችን ተግባራዊ ለማድረግ የክትትል፣ የቁጥጥርና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥርዓት መዘርጋታቸውን በተመለከተ፣

**የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ በአገር አቀፍ ደረጃ የህብረት ስራ ፖሊሲ ቀርጾ አፈፃፀሙን መከታተሉን በተመለከተ፣**

8. በቀድሞው ኦዲት ወቅት እንደታየው የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ እስከ 2003 ዓ.ም የህብረት ስራ ፖሊሲን ለማስፀደቅ በዕቅድ ከመያዝ ባለፈ በአገር አቀፍ ደረጃ የህብረት ስራ ፖሊሲ እንዲቀረፅ አላደረገም ነበር፡፡

9. ስለሆነም ህብረተሰቡ ስለ ህብረት ሥራ በቂ ግንዛቤ እንዲኖረውና ትኩረት እንዲሰጠው ለማድረግ እንዲሁም ለህብረት ስራ ማህበራት አቅጣጫ እና እድገት አመላካች እንዲሆን የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ በአገር አቀፍ ደረጃ የህብረት ስራ ፖሊሲ ቀርጾ አፈፃፀሙን ሊከታተል እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ የነበረ ሲሆን በዚሁ መሰረት የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ኤጀንሲው የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገባ ይገባል፡፡

10. የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡ ኤጀንሲው በላከው የድርጊት መርሃ ግብር ላይ አዲስ የፖሊሲ ስራ ከመስራት በ2007 በጀት ዓመት በየቦታው የተበታተኑ ህብረት ስራን የተመለከቱ የፖሊሲ ሀሳቦችን የማሰባሰብ እና ሰነዱን በአንድነት በማድረግ ለተጠቃሚዎች እንዲደርስ ማድረግ እና በሰነዶቹ ላይ ግንዛቤዎችን የመፍጠር ስራዎች እንደሚሰሩ ማቀዳቸውን ገልፀዋል፡፡

11. በክትትል ኦዲቱ ወቅት በተለያዩ ቦታዎች ተበታትነው የሚገኙ የህብረት ሥራ ማህበራትን የሚመለከቱ የፖሊሲ ሃሳቦች ተሰባስበው የተቀመጡ መሆኑን እንዲሁም በ2009 እራሱን የቻለ የህብረት ስራ ማህበራት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ እያተዘጋጀ መሆኑን እንዲሁም ረቂቅ ላይ መድረሱን ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

12. ስለጉዳዩ የፅ/ቤቱ ኃላፊዎች በቃል መጠይቅ በሰጡት ምላሽ በተለያዩ የአገሪቱ ፖሊሲ ላይ ስለ ህብረት ስራ ማህበራትን የሚመለከተውን ሃሳቦች በማሰባሰብ ማስቀመጥ መቻሉን እንዲሁም በ2009 እራሱን የቻለ የህብረት ስራ ፖሊሲ እና ስትራቴጂ እያተዘጋጀ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

**የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ ለህብረት ስራ ማህበራት የሚሰጠውን ድጋፍ በረጅምና በአጭር ጊዜ እቅድ ውስጥ ማካተቱን እና ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፣**

13. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ከ2000-2002 ዓ.ም እና ከ2003-2007 ዓ.ም ባዘጋጃቸው ስትራቴጂክ እቅዶች ውስጥ 2204 መጋዘኖች ተገንብተው ለህብረት ስራ ማህበራት ለመስጠት፣ 3 የህብረት ስራ ባንኮችንና 2 ኢንሹራንሶችን ለማቋቋም፣ የግብይት መረጃ ልውውጥ ስርአትና ትስስር ለመዘርጋት እንዲሁም የስልጠና ፍላጎት ጥናት በ2001 እና በ2003 ለማጥናት እቅድ ቢይዝም ተግባራዊ አለማድረጉ ፣ ከ2001-2003 ዓ.ም ባሉት የዕቅድ ክንውን ሪፖርቶች ላይ በአለም አቀፍ የስራ ድርጅት (ILO) በየጊዜው የሚወጡ ውሳኔዎችንና ስምምነቶችን ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ተግባራዊ ለማድረግ፣ የህብረት ስራ ማህበራትን እንቅስቃሴ ሊያግዙ የሚችሉ ፕሮጀክቶችን ለማዘጋጀት እና በፌዴራል ደረጃ ህብረት ስራ ማህበራትን (በመሰረታዊ፣ በዩኒየን እና በፌደሬሽን) ለማደራጀት በየአመቱ እቅድ ቢይዝም አለማከናወኑ በቀድሞው ኦዲት ወቅት ታውቆ ነበር፡፡

14. በዚሁ መሰረት ኤጀንሲው በሚያዘጋጀው የስትራቴጅክ እቅድ ውስጥ ለማህበራት በሚሰጠው ድጋፍ ዙሪያ የሚሰራውን ሥራ በማካተት ተግባር ላይ መዋላቸውን ሊከታተል፣ በስትራቴጂክ እቅድ የተካተቱ ተግባራትን በዓመታዊ እቅድ በመያዝ ሊያከናውን እንዲሁም በየበጀት ዓመቱ ላልተከናወኑ ተግባራት እርምጃ ሊወስድ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ የነበረ ሲሆን በተጨማሪም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ኤጀንሲው የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገባ ይገባል፡፡

15. የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡ ኤጀንሲው በላከው የድርጊት መርሃ ግብር ላይ በቀጣይ ለባንክና ኢንሹራንስ ስራ የሚፈቅድና የሚያመች ህግ እንዲኖር ህብረት ስራ ማህበራት አዋጅ 147/91 ለማሻሻል መታቀዱን በዚህም መሰረት አዋጁን ለማሻሻል ግብዓቶች የማሰባሰብ ስራዎች እየተሰሩ እንደሚገኝና ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ የህብረት ስራ አዋጅ ውስጥ ተካቶ እንዲሻሻል ጥረት ማድረግ፣ ችግሩን በዘለቄታ ለመፍታት

እንዲቻል ከብሔራዊ ባንክ፣ ከህዝብ ተወካዮች እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመወያየት በዚህ ረገድ ያለውን ችግር ለመፍታት እንደሚሰራ ገልፀዋል፡፡

16. በክትትል ኦዲቱ ወቅት

- የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ባንክና ኢንሹራንስን በተመለከተ ህግ አጥንቶ ለጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ ማቅረቡ፤
- ኤጀንሲው በአለም አቀፍ የስራ ድርጅት (ILO) በየጊዜው የሚወጡ ውሳኔዎችንና ስምምነቶችን ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ተግባራዊ ማድረግን በተመለከተ የአለም ስራ ድርጅት ከአለም የህብረት ስራ ማህበራት ጋር በመሆን የሚወጣቸውን ነጥቦች በአዲሱ አዋጅ 985/2009 ዓ.ም ላይ ለማካተት ከ ILO እና ICA ግብአት መጠየቁ ፤
- የፕሮጀክቶችን ቀረጻ በተመለከተ በኤጀንሲው የተቀረጸ አግሮ ፕሮጀክት በአማራ ፣ ትግራይ፣ ኦሮሚያ እና ደቡብ ክልሎች በግብርና ምርቶች ላይ ለተሰማሩ ህብረት ስራ ማህበራት ላይ እየተተገበረ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ይሁን እንጂ በክትትል ኦዲቱ ወቅት

- ኤጀንሲው እንደየህብረት ስራ ማህበራቱ ፕሮጀክቶች ያልቀረጸ እና ከግብርና ውጪ ላሉ ህብረት ስራ ማህበራት የተቀረጹ ፕሮጀክቶች አለመኖራቸው፣ ለግብርና ነክ ህብረት ስራ ማህበራት የተቀረፀው ፕሮጀክትም በሁሉም ክልሎችና ህብረት ስራ ማህበራት ተደራሽ አለመሆኑ፣ እንዲሁም የኦሮሚያ እና አዲስ አበባ ህብረት ስራ ማስፋፊያ ኤጀንሲ የህብረት ስራ ማህበራትን ለመደገፍ የሚረዱ ፕሮጀክቶችን ለመቅረፅ የሚረዳ መዋቅር የሌላቸው መሆኑን፣

- ኤጀንሲው በአንደኛ እድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (ከ2003 እስከ 2007 ዓ.ም) ባዘጋጃቸው እቅዶች ውስጥ 2204 መጋዘኖች እንዲሁም 3 የገበያ ማዕከል ገንብቶ ለህብረት ስራ ማህበራት ለመስጠት ቢያቅድም 44 (2 %) መጋዘኖችን ብቻ የፈጸመ መሆኑ፣ እንዲሁም ኤጀንሲው በሁለተኛው እድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በ2008 ዓ.ም 482 እና በ2009 ዓ.ም 482 መጋዘኖች ለህብረት ስራ ማህበራት ለመስራት ቢያቅድም በ2008 እና 2009 ዓ.ም በቅደም ተከተላቸው 12 (2.48%) እና 157 (32.57%) መጋዘን ብቻ መገንባቱን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

17. ስለጉዳዩ የፅ/ቤቱ ኃላፊዎች በክትትል ኦዲቱ በቃለ መጠይቅ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ ፕሮጀክቶች ሲቀረፁ 1ኛ በህብረት ስራ ኤጀንሲ 2ኛ በመንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች 3ኛ በመንግስት እንደ ፕሮግራም የሚቀረፁ እና ህብረት ስራ ኤጀንሲም የሚሳተፍባቸው መሆናቸውና ለህብረት ሥራ ማህበራት የተቀረጹ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ ህብረት ስራ ኤጀንሲ የትኩረት አቅጣጫዎቹ ግብርና፣ የገንዘብ ቁጠባና ብድር እና ሸማቾች ላይ ሲሆን ያላቸው የፕሮጀክት ባለሙያ 1 ብቻ መሆኑን የስራ ድርሻውም ፕሮጀክቶችን መቅረፅ እና ያሉትን ፕሮጀክቶች መከታተል እንደሆነ በዚህም በህብረት ስራ ኤጀንሲ የተቀረፁ ፕሮጀክቶች አናሳ መሆናቸው ነገር ግን ከሌሎች አካላት ጋር በመተባበር የተቀረፁ ፕሮጀክቶች ላይ የተሰሩ ስራዎች ትኩረት ሊሰጣቸው እንደሚገባ ገልፀው እና የተቀረፁ ፕሮጀክቶች

- 1ኛ መካከለኛ የገጠር ፋይናንስ ፕሮግራም (rural financial intermediate program /RUFIP) ፕሮጀክት፣
- 2ኛ የአርብቶአደሩ ማህበረሰብ ልማት ፕሮጀክት (Pastoral community development project/ PCDP)፣
- 3ኛ የቤተሰብ ሀብት/ጥሪት ማሳደጊያ ፕሮግራም (household asset building program HABP) ፕሮጀክት፣
- 4ኛ የግብርና እድገት ፕሮግራም (agricultural growth program AGP) ፕሮጀክት፣
- 5ኛ AGRA የአፍሪካን ግብርና የማሳደግ (growth African agriculture) ፕሮጀክት

ሲሆኑ RUFIP፣ PCDP እና HABP ፕሮጀክቶች የገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበራት ላይ እንደሚሰሩ እንዲሁም AGP እና AGRA ፕሮጀክቶች ደግሞ ግብርና ላይ የሚሰሩ እንደሆኑ ፤ መጋዘን ግንባታን በተመለከተ በመንግስት፣ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እና በህብረት ስራ ማህበራት በራሳቸው የሚገነቡ መሆናቸውን መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች በ 4ቱ ክልሎች የታቀዱ 44 የመጋዘን ግንባታዎች ሙሉ ለሙሉግንባታቸው መጠናቀቁን እንዲሁም ህብረት ስራ ኤጀንሲ በእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዱ የተቀመጠውን 2000 መጋዘን ለመገንባት የ5 ቢሊየን ብር ፕሮግራም ቀርፆ ለመንግስት የበላይ አካላት ማቅረባቸውን ነገር ግን ያለፀደቀላቸው መሆኑን የገበያ ማዕከላት ግንባታ በተመለከተ ህብረት ስራ ኤጀንሲ እንደ እቅድ ያስቀመጠው ክልሎች እንዲገነቡ

አቅጣጫ ከማስቀመጥ አንፃር እንጂ ሙሉ ለሙሉ በፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ይገነባሉ ተብለው የታሰቡ አለመሆናቸውን ህብረት ስራ ኤጀንሲም መጠየቅ ካለበት ግንባታዎቹን ክልሎች ስለማከናወናቸው ክትትሉ ምን እንደሚመስል መሆን እንዳለበት ገልፀዋል፡፡

18. የኤጀንሲው ኃላፊዎች ይህንን ይበሉ እንጂ ከአግራ ፕሮጀክት በስተቀር ከላይ የተገለፁ ፕሮጀክቶች በአገር አቀፍ ደረጃ በሌሎች አካላት (በግብርና ሚኒስቴር ፣ በፌደራል ጉዳዮችና አርብቶ አደሮች ሚኒስቴር፣ IFAD(መንግስታዊ ያልሆነ ተቋም)) የተቀረፁ እንጂ በስትራቴጂክ እቅዳቸው መሰረት በህብረት ስራ ኤጀንሲ ያልተቀረፁና የእነርሱ ፕሮግራሞች ባለመሆናቸው እንዲሁም የመጋዘን ግንባታን በተመለከተ ለመንግስት የበላይ አካል ፕሮግራም ቀርፀው ማቅረባቸውን እንዲሁም የገበያ ማዕከላትን በተመለከተ ክልሎች ግንባታ ስለማከናወናቸው ክትትል ያደረጉበትን ማስረጃ ያላያያዙ እና የግንባታ አፈፃፀሞቹም አነስተኛ በመሆናቸው የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

19. የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ የህብረት ስራ ማህበራትን ሊያግዝ የሚችል እንደየ ህብረት ስራ ማህበራት አይነት ፕሮጀክቶችን በተጠናከረ መልኩ ቀርፆ ተግባር ላይ ባለመዋሉ ህብረት ስራ ማህበራት እንዳይጠናከሩ የሚያደርግ ሲሆን ኤጀንሲው በእቅዱ መሰረት መጋዘኖችን እና የገበያ ማዕከላትን ገንብቶ ለህብረት ስራ ማህበራት ባለማስተላለፉ ህብረት ስራ ማህበራት ከአባላትና አባል ካልሆኑ አርሶ አደሮች ለሚሰበስቡት ምርት  የሚያከማቹበት እንዲሁም ምርታቸውን ለገበያ የሚያቀርቡበት ቦታ  ቦታ በማጣት እንዲቸገሩ  ያደርጋል፡፡

**የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ ህብረት ስራ ማህበራት ከመደራጀታቸው በፊት እንዲሁም ከተደራጁ በኋላ እንዲያድጉ ጥናትና ምርምር ማድረጉን እና የክልል ማስፋፊያ አካላት ጥናት እንዲያደርጉ እገዛ ማድረጉን በተመለከተ፣**

20. በቀድሞው ኦዲት ወቅት ክልሎች ህብረት ስራ ማህበራትን በብዛት የሚያደራጁ ቢሆንም የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ በየክልሉ ለሚገኙ አደራጅ ባለሙያዎችን የአዋጭነት ጥናት እንዲያጠኑ በተግባር በማሳየት እገዛ ያላደረገ መሆኑ፤ በኦዲቱ በናሙና በታዩት የክልል ኅብረት ሥራ ማስፋፊያ አካላት የሶሽዩ ኢኮኖሚ ጥናት እንዲያጠኑ የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ እገዛ ያላደረገላቸው መሆኑን፣ በክልል በዞኖችና ወረዳዎች የሚገኙ ህብረት ስራ ማህበራት አደራጁ በራሱ በመሰለው

አስተያየት የሚያደራጅ እንጂ ለጥናት ተብሎ የተዘጋጀ መመሪያ አለመኖሩ፣ በክልሎች የሚሰራው የአዋጭነት ጥናት ወጥነት የሌለው መሆኑ (በቅጽ፣ ከሌላ ጥናት ጋር አንድ ላይ በማድረግ፣ የንግድ እቅድን እንደ አዋጭነት በመውሰድ መሰራቱ)፣ እንዲሁም ህብረት ስራ ኤጀንሲ ባሕላዊና ሀገር በቀል የራስ አገዝ ማህበራት (እድር፣ መረዳጃ ማህበር ወዘተ) ወደ ዘመናዊ የህብረት ስራ ማህበራት የሚያድጉበትን ጥናት እና ምርምር አለማድረጉ ታውቆ ነበር፡፡

21. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ህብረት ስራ ማህበራት ከተደራጁ በኋላ ለኪሳራ እንዳይጋለጡ፣ ለአባሎቻቸውና ለህብረተሰቡ ቀጣይነት ያለው አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴያቸውን ለመገምገም እንዲያስችል እና ውጤታማ ለመሆን የሚያስችላቸውን የህብረት ስራ ዘርፍ ለመምረጥ ከመደራጀታቸው በፊት የሶሽዩ ኢኮኖሚ ጥናትና የአዋጭነት ጥናት ሊያጠና ወይም ክልሎች እንዲያጠኑ እገዛ ሊያደርግ እንዲሁም በአዋጅ በተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት መሰረት የማህበራትንና የአባላትን አቅም ለማጎልበትና የአሰራር ስርዓታቸውን ለማሻሻል በባህላዊና ሀገር በቀል ደረጃ ያሉትን እድር፣ መረዳጃ ማህበራት ወ.ዘ.ተ. ወደ ዘመናዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያድጉበትን ጥናትና ምርምር ሊያከናውን እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ የነበር ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ኤጀንሲው የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገባ ይገባል፡፡

22. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡ ኤጀንሲው በላከው የድርጊት መርሃ ግብር ላይ በ2005 ዓ.ም በዕቅድ ተይዞ የአዋጭነት ጥናት የትግበራ ማኑዋል ሰነድ ተዘጋጅቶ በተወሰኑ ህብረት ስራ ማህበራት ላይ ሙከራ የተደረገ እና ስራው ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ እየተከናወነ መሆኑን፣ ከመስከረም 2007 ጀምሮ በቀጣይ ሰነዱ ላይ ከፌደራል እስከ ቀበሌ ላሉት ባለሙያዎች በሰነዱ ላይ ስልጠና በማዘጋጀት ግንዛቤያቸው እንዲያድግና ስራው ተጠናክሮ እንዲቀጥል እንደሚደረግ ገልፀዋል፡፡

23. በክትትል ኦዲቱ ወቅት

- የሶሺዮ ኢኮኖሚ እና አዋጭነት ጥናት በኤጀንሲው የህብረት ሥራ ማስፋፊያ ዳይሬክቶሬት ደረጃ 2005 ዓ.ም ላይ መጠናቱ መሻሻል የታየበት ተግባር መሆኑ፣

ይሁን እንጂ በክትትል ኦዲቱ ወቅት

* ባሕላዊና ሀገር በቀል የራስ አገዝ ማህበራት (እድር፣ መረዳጃ ማህበር ወ.ዘ.ተ.) ወደ ዘመናዊ የህብረት ስራ ማህበራት ሊያድጉ የሚችሉበት ጥናት እና ምርምር ሥራ አለመከናወኑ፤
* በኤጀንሲው የህብረት ሥራ ማስፋፊያ ዳይሬክቶሬት ደረጃ የተጠናው የሶሺዮ ኢኮኖሚ እና አዋጭነት ጥናት እንደ ሀገር አቀፍ ተገምግሞና ጸድቆ በመመሪያ ያልወጣና ለክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ያልተሰራጨ መሆኑ፣
* በክትትል ኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ በአዲስ አበባ ከተማ፣ ኦሮሚያ እና አማራ ክልል የዞንና የወረዳ ህብረት ስራ ማህበራት ማስፋፊያ አካላት የሶሺዮ ኢኮኖሚ ጥናት ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ቀን ድረስ አጥንተው የማያውቁ መሆኑ ፣
* በደቡብ ክልል 21፣ በኦሮሚያ ክልል 1፣ በአዲስ አበባ ከተማ 10፣ በሃረር 7፣ ድሬዳዋ 10፣ አማራ 8፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ 24፣ ጋምቤላ 6፣ ሶማሌ 37፣ አፋር 27 እና ትግራይ ክልል 27 ህብረት ስራ ማህበራት የአዋጭነት ጥናት ያልተጠናላቸው መሆኑ ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት መቻሉ፣ ዝርዝሩ **በአባሪ 2 ተያይዟል፡፡**
* በኦሮሚያ ክልል በናሙና ከታዩ ህብረት ስራ ማህበራት የአዋጭነት ጥናት የተጠናላቸው ቢሆንም ወጥ የሆነ የአዋጭነት ጥናት ፎርማት /መመሪያ/ ባለመኖሩ የተለያየ አሰራር መኖሩ፣ እንዲሁም በአማራ ክልል በናሙና በታየው በባህር ዳር ከተማ የሚገኘው ዘንባባ የንብ ውጤቶች ልማትና ግብይት ህብረት ስራ ዩኒየን ሲቋቋም የአዋጭነት ጥናት ባለመካሄዱ ዩኒየኑ በተደጋጋሚ ለኪሳራ እየተዳረገ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

24. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች በቃለ መጠይቅ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት ምላሽ የሶሺዮ ኢኮኖሚክ ጥናት በተመለከተ ለ4ቱ ድጋፍ የሚሹ ክልሎች ተጠንቶ መሰራጨቱን በሌሎች ክልሎች ላይ ግን በኤጀንሲው እንደ መመሪያ አውርደው ለክልል ባለሙያዎች ስልጠና ለመስጠት ቢያቅዱም ባለፈው አመት በአገሪቱ በነበረው አለመረጋጋት ለማሰራጨት እንዳልቻሉ እንደ ክፍተትም የሚወስዱት መሆኑን ፤ ባህላዊ እራስ አገዝ ማህበራትን ወደ ዘመናዊ ህብረት ስራ ማህበራት መለወጥን በተመለከተ ያልተሰራ እና ያላቸው እሴት የተለያየ በመሆኑ ለወደፊትም ይሰራል ብለው እንደማይጠብቁ ሙሉ ለሙሉ ወደ ህብረት ስራ መቀየር ላይ ሳይሆን ባህላዊ ተቋማቱ በህብረት ስራ ማህበራት ላይ ተሳትፎ

እንዲኖራቸው ውይይት እያደረጉበት መሆኑን ባረቀቁት የህብረት ስራ ፖሊሲ እና ስትራቴጂም ባህላዊ ማህበራቱን ወደ ዘመናዊ ህብረት ስራ ማህበራት መቀየሩን ከኃላፊነታቸው ያወጡት መሆኑን እና ሲፀድቅም የሚስተካከል መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም ለኤጀንሲው በተላከው ረቂቅ የክትትል ኦዲት ሪፖርት ምላሽ ላይ በህብረት ስራ አደረጃጀት መመሪያ ውስጥ እንዴት እንደሚደራጅ የሚያሳይ ግልጽ የሆነ የሶሺዮ ኢኮኖሚ ጥናት ተካቶበት እንደተቀመጠ ነገር ግን ባለሙያው የተሻለ ግንዛቤ ለመፍጠር ዘርዘር ተብሎ እንዲቀርብ ሲባል የሶሺዮ ኢኮኖሚና አዋጭነት ጥናት ማኑዋል በፌደራል እንዲዘጋጅ እንደተደረገና የስልጠና ማኑዋል በማዘጋጀት ስልጠና የተሰጠና ሰነዱም የተሰራጨ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

25. የፅ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህንን ይበሉ እንጂ በኤጀንሲው ድጋፍ በሚሹ ክልሎች ተሰራ የተባለው ሶሺዮ ኢኮኖሚክ ጥናት በአፋር ክልል በ1995 ዓ.ም የተሰራና ያልተሻሻለ በመሆኑና ፣ በኤጀንሲው ህብረት ስራ ማስፋፊያ ዳሬክቶሬት በአንድ ባለሙያ ጥቅምት በ2005 ዓ.ም የተሰራው የሶሺዮ ኢኮኖሚ እና አዋጭነት ጥናት ማኑዋል እስከ አሁን በኤጀንሲው ደረጃ ሰነዱ ተገምግሞና ዳብሮ እንደ መመሪያ ወርዶ ለክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ያልተሰራጨ በመሆኑ የቀረበውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግረዋል፡፡

26. የሶሺዮ ኢኮኖሚ እና የአዋጭነት ጥናት ባለመጠናቱ የህብረት ስራ ማህበራት ቀጣይነት ባለው መልኩ ውጤታማ በመሆን ለአባሎቻቸው የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት እንዳይሰጡ እና ለኪሳራ በመጋለጥ ህልውናቸውን እንዲያጡ የሚያደርግ እንዲሁም ኤጀንሲው በፌዴራልም ሆነ በክልል የሚገኙ ህብረት ስራ ማህበራት ከባህላዊ ወደ ዘመናዊ ህብረት ስራ ማህበር ተለውጠው ውጤታማ እንዳይሆኑ እንቅፋት ይሆናል፡፡

**የህብረት ስራ ማህበራት በፌዴራል እና በክልል ስለመደራጀታቸው እንዲሁም የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ በአገር አቀፍ ደረጃ የህብረት ስራ ሊግ ማቋቋሙን በተመለከተ፤**

27. በኤጀንሲውና በክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት እስከ 2003 ዓ.ም 38,703 ህብረት ሥራ ማህበራት የተደረጁ ቢሆንም ኤጀንሲው በፌዴራል ደረጃ ያቋቋመው አንድ መሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበር ብቻ መሆኑን ዩኒየንና ፌዴሬሽን አለማቋቋሙን፣ ይህንንም በተመለከተ ኤጀንሲው ከክልሎች ጋር ስምምነት ላይ ያልደረሰ መሆኑን፣ በክልል ደረጃ በኦሮሚያ ሁለት ፌዴሬሽን፣ በትግራይና በደቡብ ክልሎች አንድ አንድ ኀብረት ሥራ ፌዴሬሽን መቋቋሙ፣ በአገር አቀፍ ደረጃ

የህብረት ስራ ሊግ አለመቋቋሙ ፣ እስከ ግንቦት 2003 ዓ.ም ልዩ ድጋፍ በሚሹ ክልሎች (ቤኒሻንጉል፣ ጋምቤላ፣ ሶማሌና አፋር) ከተደራጁት 1539 ኅብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ከ2001-2002 ዓ.ም 3 ህብረት ስራ ማህበራትን ብቻ ያደራጀ ሲሆን በ2003 ስለማደራጀቱ መረጃ በኦዲቱ ወቅት አለመቅረቡ የቀድሞው ኦዲት ግኝቶች ነበሩ፡፡

28. የህብረት ስራ ማህበራት ለአባላቶቻቸው እና ለህብረተሰቡ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት መፋጠን የሚያበረክቱትን አስተዋጽኦ በተሻለ ደረጃ ለመወጣት እና ከአለም አቀፍ የሕብረት ሥራ ማህበራት ጋር በማስተሳሰር የማህበራትንና የአባላትን አቅም ማሳደግ እንዲያስችል በአገር አቀፍ ደረጃ የሕብረት ሥራ ፌዴሬሽንና የህብረት ስራ ሊግ ሊያቋቁም እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ በተጨማሪም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ኤጀንሲው የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገባ ይገባል፡፡

29. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡ ኤጀንሲው በላከው የድርጊት መርሃ ግብር እቅዱ ላይ በክልል ደረጃ ያሉት ፌደሬሽኖች የማይፈቱትን አይነት ችግር ሳይለይ፣ ብቁ ህብረት ስራ ማህበራትን ሳይፈጠር፣ የተጠቀሱትን ስራዎች አስፈላጊነት፣ ያለውን አሰራርና ስለሚያከናውናቸው ተግባራት በቅድሚያ ሳይጠና እና ስርዓት ሳይቀመጥላቸው በወቅቱ የህብረት ስራ ሊግ ለማቋቋም ካለው ፍላጎት ብቻ ለማደራጀት እንቅስቃሴ የተጀመረ መሆኑን፣ ለወደፊት ክልሎችን የማብቃት ስራ ተጠናክሮ እንደሚሰራ ፣ የህብረት ስራ ማህበራት በጋራ ማደራጀትም ሆነ ማጠናከር እንዲሁም የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን የመስጠት ስራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ፣ ከዚህም በመቀጠል የህብረት ስራ ፌዴሬሽን ለማደራጀት በአስፈላጊነቱ ላይ ጥናት በማድረግ አሰራር ስርዓት በማስቀመጥ ከ2010 ዓ.ም በኃላ ለዚህ የሚያበቃ ስራ እንደሚሰራ ገልጸዋል፡፡

30. ይሁን እንጂ በክትትል ኦዲቱ ወቅት

- ኤጀንሲው በክዋኔ ኦዲት ግኝት መሰረት በድርጊት መርሃ ግብሩ ላይ የአዋጭነት ጥናት በማጥናት ከ2009 ዓ.ም በኃላ በሀገር አቀፍ ፌዴሬሽን ለማቋቋም እንደሚሰራ ያስቀመጠ ቢሆንም በ2ኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ላይ ሀገር አቀፍ ፌዴሬሽን በዕቅድ ያልያዘ መሆኑና በፌዴራል ደረጃ የተቋቋመ ፌዴሬሽን አለመኖሩ፣

- ድጋፍ በሚሹ ክልሎች ከተቋቋሙ ህብረት ስራ ማህበራት ኤጀንሲው ያቋቋመው በአፋር፣ ሶማሌ፣ ቤኒሻንጉል ጉምዝ እና ጋምቤላ ክልል በቅደም ተከታላቸው ካላቸው 966፣ 3024፣ 846 እና 807 የህብረት ሥራ ማህበራት በቅደም ተከተላቸው 83፣ 123፣ 84 እና 79 ብቻ መሆኑ ፣
- በአገር አቀፍ ደረጃ የህብረት ስራ ሊግ አለመቋቋሙ መሆኑን በክትትል ኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

31. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በቃለ መጠይቅ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት ምላሽ በአገር አቀፍ ደረጃ መሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራትን እና ፌደሬሽን ለማቋቋም በተለያዩ ክልሎች ካሉ ህብረት ስራ ማህበራት እንዲሁም ከተመሰረቱ ህብረት ስራ ዩኒየኖች ፍላጎት የሚመጣ እንጂ ህብረት ስራ ኤጀንሲ በራሱ ከላይ የሚያወርደው እንዳልሆነ ነገር ግን ፌዴሬሽን ለማቋቋም ጥናት አጥንተው ክልሎችን ቢያወያዩም ሁሉም ክልሎች የጋራ ስምምነት ላይ ባለመድረሳቸው ሊቋቋም አለመቻሉን፣ ሊግን በተመለከተ ከዚህ ቀደም ፌዴሬሽኖች ከተቋቋሙ በኃላ ይቋቋማሉ የሚል እሳቤ የነበረ መሆኑን አሁን ላይ ግን ፌዴሬሽኖች ባይቋቋሙም በአገር አቀፍ ደረጃ ሊግን ለማቋቋም በሃሳብ የተያዘና ወደ ፊት የሚሰራበት መሆኑን፣ ድጋፍ በሚሹ ክልሎች በኤጀንሲው ማደራጀትን በተመለከተ የተሰሩ ስራዎች እንዳሉ ሆነው ኤጀንሲው ካለው አነስተኛ የሰው ኃይል አንፃር ክፍተቶች እንደተፈጠሩ ወደ ፊት አጠናክረው የሚሰሩ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

እንዲሁም በረቂቅ የክትትል ኦዲት ሪፖርት ላይ በተሰጠው ምላሽ በፌደራል ደረጃ የሚከናወኑ የአቅም ግንባታ ስራዎች እንደተጠበቁ ሆነው ድጋፍ የሚሹ ክልሎች ራሳቸውን ችለው ማደራጀት እስከሚችሉ ድረስ በስፍራው ከእነሱ ጋር በጋራ በመሆን በማሳየት የማደራጀት አቅማቸውን ለማሳደግ እንዲቻል ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች የተለየ ድጋፍ በመስጠት እንዲደራጁ እንደተደረገና ከዚህም ጎን ለጎን አብዛኛው የተደራጁ ህብረት ስራ ማህበራትም በፌደራሉ በተደረገው ድጋፍ ጭምር እንደሆነ እንዲሁም የህብረት ስራ ማህበራት ፌደሬሽን ለማደራጀት በመጀመሪያ ችግሩና ፍላጎቱ ከክልሎች መምጣት እንደሚኖርበት ምክንያቱም ከሚካሄደው ፌደራሊዝም ስርዓት አንጻር ፌደሬሽን ማደራጀት አንድ ኢኮኖሚያዊ ህብረተሰብ መፍጠር በመሆኑ የክልሎችና የመደራጀት ፍላጎት ከሆነ አስፈላጊነቱ በመለየት ወደ ማደራጀቱ ለመሄድ የስምምነት ችግር እንደሌለ ገልጸዋል፡፡

32. ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ ፌዴሬሽን ለማቋቋም በ2001 ዓ.ም አገር አቀፍ የህብረት ስራ ፌደሬሽን ለመመስረት የተደረጉ ጥረቶች፣የታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች እና ሊወሰዱ የሚችሉ የመፍትሄ ሀሳቦች በሰነድ ተዘጋጅቶ የቀረበ ቢሆንም ሰነዱን መነሻ በማድረግ አገር አቀፍ የህብረት ስራ ፌደሬሽን ሊመሰረት ያልቻለበትን ምክንያት በመለየትና ተጨማሪ ጥናት በማድረግ ለችግሮቹ መፍትሄ በመስጠት ወደ ተግባር ከመግባት ይልቅ በ2ኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ላይ ሀገር አቀፍ ፌዴሬሽን ማቋቋምን በተመለከተ ሙሉ በሙሉ በኤጀንሲው ዕቅድ የተያዘ በመሆኑ የሰጡትን ምላሽ ለመቀበል አልተቻለም፡፡

33. በፌዴራል ደረጃ ፌደሬሽን ባለመቋቋሙ ምክንያት አገሪቱ ከዓለም አቀፍ የህብረት ስራ ህብረት (International Cooperative alliance ) ማግኘት የሚገባትን የአባልነት ጥቅሞችና የልምድ ልውውጥ እንዳታገኝ ማነቆ ከመሆኑም በላይ በክልል ደረጃ የተደራጁት ፌደሬሽኖች በቅንጅት እንዳይሰሩና ሀገራዊ ትስስር እንዳይፈጥሩ በማድረግ ህብረት ስራ ማህበራት በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የገበያ ትስስር ድጋፍ ማግኘት እንዳይችሉና ከምርት ግብይት ተጠቃሚ እንዳይሆኑ፣ እንዲሁም ከጅምላ አከፋፋዮች ጋር ቀጥተኛ ትስስር መፍጠር እንዳይችሉ ያደርጋል፡፡ በአገር አቀፍ ደረጃ የህብረት ስራ ሊግ ባለመቋቋሙ ስለ ህብረት ስራ በአገር አቀፍም ሆነ በአለም አቀፍ የማስተዋወቅ ፣ ተወካይ ሆኖ መቅረብ፣ ፖሊሲዎችን ማዘጋጀት እና ለህብረት ስራ ፈንድ የማፈላለግ የመሳሰሉት ስራዎች ተጠናክረው እንዳይሰሩ እንቅፋት ይሆናል፡፡

### ኤጀንሲው የሥልጠና ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ

34. የፌዴራል ሕብረት ሥራ ኤጀንሲ በፌዴራል ደረጃ የህብረት ስራ ማሰልጠኛ ተቋም አለማቋቋም፣ በፌዴራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ የሁሉንም ክልል የስልጠና ፍላጐት ጥናት አለማጥናት፣ ህብረት ስራ ማህበራት እና ማስፋፊያ አካላት በአብዛኛው ስልጠና አለማግኘት ስልጠና ያገኙትም ቢሆኑ እለታዊ ችግሮችን ለመፍታት እንጂ የተቀናጀ እና ጥናትን መሠረት ያደረገ ችግርን በዘላቂነት እንዲፈታ የእውቀትና የክህሎት ክፍተት ለመሙላት ታስቦ የሚሰጡ ስልጠና አለመኖር፤ በፌዴራል ደረጃ እና በክልል የሚሠጡ ስልጠናዎችን ተመጋጋቢ አለማድረግ እና ድግግሞሽን (ተመሣሣይ ስልጠና ለተመሣሣይ ሰልጣኞች መስጠትን) አለማስቀረት፤ የስልጠና ውጤት የሚለካበት ስርዓትም በኤጀንሲው አለመዘርጋት እንዲሁም በክልል ኅብረት ሥራ ማስፋፊያ አካላት የተሰጡ ስልጠናዎች ያመጡት ውጤት አለመለካት በቀድሞው ኦዲት ወቅት የታዩ ክፍተቶች ናቸው፡፡

35. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲና የህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት የህብረት ስራ ማህበራትን አቅም ለማጎልበት፣ በፌዴራል እና በክልል የሚሰጡ ስልጠናዎችን ተመጋጋቢ ለማድረግ፣ የስልጠና ድግግሞሽን ለማስቀረት እና የሚሰጡ ስልጠናዎች የሚያመጡትን ውጤት ለመለካት ተናበው ሊሠሩ እንደሚገባ እንዲሁም ኤጀንሲው የስልጠና ክትትል ስርዓት በመዘርጋት የክልል ኅብረት ሥራ ማስፋፊያ አካላት ለሚሰጡት ስልጠና የስልጠና ፍላጐት ጥናት እንደሚያደርጉ ሊከታተልና በየጊዜው የሚሠጡ ስልጠናዎች በሠልጣኙ እና በኅብረት ሥራ ማህበራት ላይ ያመጡትን ውጤት ለማወቅና ለቀጣይ የሚሰጡ ስልጠናዎችን ለማቀድ እንዲያስችል ስልጠናዎች ያመጡትን ውጤት የሚገመግምበትና የሚለካበት ስርዓት ሊኖረው እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ኤጀንሲው የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገባ ይገባል፡፡

36. የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡ ኤጀንሲው በላከው የድርጊት መርሃ ግብር በተቋሙ የስልጠና፣ የስርዓተ ትምህርትና የማኑዋል የማዘጋጀት ስራ እንዲሁም ስልጠናዎች መሰጠት መጀመሩን፣ ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ በቀጣይ የውስጥ አደረጃጀቱን እና አስተዳደራዊ ስራዎችን የማጠናከርና የማደራጀት ፣የልቀት ማዕከል ሆኖ የሚያገለግል ምቹ ሁኔታ የመፍጠር ፣የተቋሙን የተጠሪነት ሁኔታዎች የማመቻቸት ፣የሚሰጡ ስልጠናዎች በልዕቀት ማዕከሉ በተጠናከረ ሁኔታ እንዲሰጡ እንዲሁም ክልሎች የስልጠና ተቋም እንዲኖራቸው የማድረግ ስራዎች እንደሚሰሩ ገልፀዋል፡፡

37. በክትትል ኦዲቱ ወቅት፡-

- የአርዳይታ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅን ወደ ህብረት ሰራ ማህበራት ማሰልጠኛ ተቋም ለመቀየር የሚቻልበትን ደንብ አስጠንቶ ለሚመለከተው አካል ማቅረቡ፣ በረጅም፣በመካከለኛና በአጭር ግዜ ለተቋሙ የሚያስፈልጉ የውስጥ ቁሳቁሶች ለማሟላት የሚያስችል የዳሰሳ ጥናት ሰነድ መዘጋጀቱ፣ ተቋሙን ወደ ስራ ለማስገባት የሚያስችል ልምድ በተሞክሮ ከውጭ ሀገራት እንዲገኝ መደረጉ፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የስልጠና ካሪኩለም መዘጋጀቱ እና የስራ መዘርዝሮች የረቀቁ መሆናቸው፣ በፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ከ2002-2005 ዓ.ም ለተሰጡ ስልጠናዎች ያመጡት ውጤት መጠናቱ፣ በፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ

አማካኝነት ከ2006-2008 ዓ.ም ለሚሰጡ ስልጠናዎች የስልጠና ፍላጎት የዳሰሳ ጥናት መደረጉ በክትትል ኦዲቱ ወቅት የተስተካከሉ ተግባራት ሆኖ ተገኝተዋል፡፡

ይሁን እንጂ በክትትል ኦዲቱ ወቅት፡-

- በአንደኛው እድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (ከ2003 - 2007 ዓ.ም) በሀገር አቀፍ ደረጃ አንድ የህብረት ስራ የስልጠና ማዕከል ለማቋቋም ታቅዶ ያልተከናወነ ሲሆን ፤በ2ኛ እድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (ከ2008 — 2012 ዓ.ም) በ2008 ዓ.ም እና 2009 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ 1 ሀገር አቀፍ እንዲሁም 2 ክልላዊ በድምሩ 3 የህብረት ስራ የስልጠና ማዕከል ለማቋቋም ታቅዶ ያልተፈጸመ መሆኑ፣
- የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ከክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ ኤጀንሲዎች ጋር በመሆን ለህብረት ስራ ማህበራት አመራር አካሎች በ2005፣ 2006፣ 2007፣ 2008 እና 2009 በጀት ዓመት በቅደም ተከተላቸው 293,394 ፣ 304,774 ፣ 85,615 ፣ 979 እና 149 የስልጠና እቅድ ቢይዝም አፈፃፀማቸው በቅደም ተከተል 85,246 (29%)፣ 25,179 (8.26%) ፣ 66,573 (77.7%) ፣ 863 (88.15%) እና 149 (100 %) መሆኑ፣ ለህብረት ስራ ማኅበራት ቅጥር ሰራተኞች በ2005፣ 2006፣ 2007፣ 2008 እና በ2009 በጀት ዓመት በቅደም ተከተላቸው 5,545 ፣ 5,942 ፣ 16,823 ፣ 203 እና 129 የስልጠና እቅድ ቢይዝም አፈፃፀማቸው በቅደም ተከተል 4,538 (81.8%)፣ 2,239 (37.6%) ፣ 5,802 (34.4%) ፣ 157 (77.3%) እና 129 (100 %) መሆኑን ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ የተቻለ ቢሆንም ለህብረት ስራ ማህበራቱ አመራር አካላትም ሆነ ቅጥር ሰራተኞች በ2008 እና በ2009 በጀት አመት ለስልጠና የተያዘው እቅድ ካሉት ህብረት ስራ ማህበራት አንፃር እና ከቀድሞው አመታት ይያዙ ከነበረው እቅድ ሲነጻጸር በጣም አናስተኛ መሆኑ፣ በአገር አቀፍ ደረጃ ለህብረት ስራ ማህበራት አባላት በ2006፣ 2008 እና በ2009 በጀት አመት ስልጠና ለመስጠት በእቅድ ያልተያዘ እና ያልተፈጸመ መሆኑ፣
- በናሙና በታዩ በአዲስ አበባ ክልል ያሉ 2 ህብረት ስራ ማህበራት የተወሰኑ ስልጠናዎችን ያገኙ ቢሆንም ስልጠናዎቹ በአብዛኛው ለባለሙያዎች ሳይሆን ለአመራር አካላት የተሰጡ፣ ስልጠና ከማግኘታቸው በፊት የስልጠና ፍላጎታቸውን ያልተጠየቁ መሆኑና ከሰለጠኑ በኃላ

ስልጠናው ያመጣው ውጤት የሚለካበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣

- በኦሮሚያ እና አማራ ክልል በዞንና በወረዳ ህብረት ስራ ኤጀንሲ በየዓመቱ የስልጠና ዕቅድ የሚታቀድ ቢሆንም በክልል ህብረት ስራ ኤጀንሲ በኩል ለስልጠና ተብሎ የሚመደብ በጀት ባለመኖሩ በዕቅድ ተይዞ በመደበኛ በጀት ስልጠና ለወረዳ ባለሙያዎች እና ለህብረት ስራ ማህበራት አመራሮችና ቅጥር ሰራተኞች ስልጠና ያልተሰጠ ሲሆን ከሌሎች ፕሮጀክቶችና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በተገኘ የበጀት ድጋፍ የሚሰጡ ስልጠናዎችን የስልጠና ፍላጎት ጥናት ላይ ተሞርኩዘው ሳይሆን የስልጠና በጀት በሚገኝበት ወቅት በተገኘው አጋጣሚዎች ወቅታዊ ችግሮችን ለመፍታት ብቻ ስልጠና የሚሰጡ መሆኑ፤ እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል በናሙና በታዩ በጅማ ዞን ኢ.ልቡ፣ እምበቆ ሁለገብ ህ/ስ/ማ (ህብረት ስራ ማህበር)፣ በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ሊበን ሁለገብ ህ/ስ/ማ፣ ጉዲና ዲነግዴ ገ/ቁ/ብ/ህ/ስ/ማ እና በአማራ ክልል በናሙና በታዩ ባህርዳር ዙሪያ ወረዳና ጎዛምን ወረዳ ጽ/ቤት እና ዘንባባ የንብ ውጤቶችና ግብይት ህ/ስ/ማ በፌደራልና በክልል ህብረት ስራ ኤጀንሲው በኩል የሚሰጠው ስልጠና ለአጭር ጊዜ በመሆኑ በተግባር ማስደገፍ አለመቻሉ የስልጠና ፍላጎት ላይ መሰረት ያላደረገ እንዲሁም ተደራሽ ባለመሆኑ በህብረት ስራ ማህበሩ ላይ የሚታየውን ክፍተቶች የማይሞላ መሆኑ በክትትል ኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

38. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች ተጠይቀው በቃል መጠይቅ፣ በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና በረቂቅ የክትትል ክዋኔ ኦዲት ሪፖርት በሰጡት ምላሽ የህብረት ስራ ስልጠና ማዕከላትን ማቋቋም በተመለከተ አርዳይታን ወደ ህብረት ስራ ማሰልጠኛ ተቋም ለመቀየር የተለያዩ ጥናቶችና ካሪኩለም ከተለያዩ ባለሙያዎች ጋር በመሆን ያዘጋጁ መሆኑን እና አሁን ላይ ከግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ ጋር ጥናቶቹን የጋራ አድርገው ለመንግስት ማቅረብ እንደቀራቸው እና በሂደት ላይ ያለ መሆኑን፣ የክልል ህብረት ስራ ልቀት ማእከላት የፌዴራሉ ካለቀ በኋላ የሚሰሩበት መሆኑን፣ ለህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት እና ማህበራት ስልጠና መስጠትን በተመለከተ በኤጀንሲው ስልጠና መስጠት ላይ ክፍተት አለ ብለው እንደማያስቡ በፌደራል ደረጃ እና በክልል ኤጀንሲ ላሉ ባለሙያዎች እንዲሁም አልፎ አልፎ ለህብረት ስራ ዩኒየኖች በስልጠና ፍላጎታቸው መሰረት ስልጠና የሚሰጥ መሆኑን፣ ህብረት

ስራ ማህበራትን ማሰልጠን የክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ኃላፊነት መሆኑን ነገር ግን ክልሎች ጋር እንደ ፌደራል በበጀትም በሰው ኃይልም ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል ብለው እንደማያምኑ እና ክፍተቶች መኖራቸውን እንዲሁም በፌደራል ደረጃ የሚሰጡ ስልጠናዎች አፈጻጸሙ እየቀነሰ የመጣው የህብረት ስራ ማህበሩ ቁጥር እየጨመረ በመምጣቱና የሚደረጉት ድጋፎች በመስፋቱ እና ለአቅም ግንባታ ያለው በጀት አለመመጣጠንና በክልል ደረጃ በቂ በጀት አለመኖር ዋና ዋና ጉዳዮች እንደሆኑ፤ ሆኖም በተመደበው በጀት መሰልጠን ያለበት ሰው ስልጠና እንዲያገኝ ከማድረጉም በላይ የተለያዩ የበጀት ድጋፍ የሚያደርጉ አካላትን በማስተባበርና በማቀናጀት ስልጠናዎች ተደራሽ ለማድረግ ጥረቶች እንደተደረጉ ፣ ከ2006-2009 ያለውን የስልጠና ውጤት ግምገማን በተመለከተ በ2009 በጀት አመት በኤጀንሲው 8 ቡድኖች ተዋቅረው በሁሉም ክልሎች ተሰማርተው መረጃዎችን እየሰባሰቡ እንደሚገኙ እና ከ2010 — 2012 ዓ.ም የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት እንደተጠና እንዲሁም ይህ የሚያሳየው የተዘረጋውን የአሰራር ስርዓት ተግባራዊ በማድረግም ሆነ ውጤትን በመለካት በኩል ምንም ክፍተት እንደሌለበት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

39. ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ ኤጀንሲው በክልል የሚሰጡ ስልጠናዎች ያሉባቸውን ክፍተቶች በማጥናት ለክልሎች ድጋፍ ማድረግ ያለበት በመሆኑ እና በታህሳስ 2009 ዓ.ም በፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ከ2006 — 2009 ዓ.ም የተሰጡ ስልጠናዎች ውጤታማነትን ለመለካት የሚያስችል ጥናት የተጠና ቢሆንም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ድረስ ተደራጅተው ከሚገኙ 80,149 መሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበር እና 381 የህብረት ስራ ዩኒየኖች መካከል ለስልጠና ውጤታማነት ጥናት በናሙና የተወሰዱ እንደ ቅደም ተከተላቸው 9 (0.011 %) መሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበር እና 18 (4.7 % ) የህብረት ስራ ዩኒየኖች ብቻ በጥናቱ መካተቱ የተሰጡ ስልጠናዎች ያመጡት ውጤትን ለመገምገም አዳጋች የሚያደርገው በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

40. በአገሪቱ የህብረት ስራ ማሰልጠኛ ባለመቋቋሙ የህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት እና ህብረት ስራ ማህበራት ወጥነት ያለውና የተጠናከረ ስልጠና እንዳያገኙ ያደርጋል፤ ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት እና ማህበራት የስልጠና ፍላጎት ጥናት መሰረት ባደረገ መልኩ ስልጠናዎች እንዲወስዱ ባለመደረጉ የሚሰጡ ስልጠናዎች የህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላትንም ሆነ ማህበራትን የክህሎት ክፍተት የማይሞሉ እንዲሆኑ የሚያደርግ ሲሆን፤ የስልጠና እቅዶች አፈፃፀም አናሳ መሆኑ ህብረት

ስራ ማስፋፊያ አካላትና ማህበራት ያሉባቸውን ክፍተቶች ሞልተው አቅማቸው እንዳይጠነክር ያደርጋል ፣ የተሰጡ ስልጠናዎች ያመጡት ውጤት የማይለካ መሆኑ ደግሞ የስልጠናዎችን ጠቀሜታ፣ ያመጡት ውጤት እንዲሁም ክፍተት እንዳይለይ ያደርጋል፡፡

**የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ ለህብረት ስራ ማህበራት ድጋፍ አሰጣጥ የሚረዱ መመሪያዎች ማዘጋጀቱንና ለህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ማሰራጨቱን በተመለከተ፣**

41. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ የህብረት ስራ ማህበራትን አዋጅችና ደንቦች ተግባራዊ ለማድረግ ካዘጋጃቸው 20 የአፈፃፀም መመሪያዎች ውስጥ ለክልሎች አስሩን መመሪያዎች የላከ ቢሆንም የተቀሩትን አስር መመሪያዎች የላከበትን ማስረጃ ያላቀረበ መሆኑ፣ በሁሉም ክልል ያሉ ህብረት ስራ ማህበራት ለጠየቁት የቦታ ጥያቄ ምላሽ የሚዘገይ ብሎም የማይመለስ መሆኑን እንዲሁም የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ህብረት ስራ ማህበራት ስለሚያወጡት ፈቃድ እና የሚከፍሉትን ቀረጥ በተመለከተ የአፈፃፀም መመሪያ አለማዘጋጀቱ በቀድሞው ኦዲት ወቅት ታውቆ ነበር፡፡

42. በህብረት ስራ አዋጅና ደንብ ላይ ማህበራት የማበረታቻ (ቦታ የማግኘት፣ ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን፣ ያለ ኢንቨስትመንትና ንግድ ፈቃድ መስራት) ምላሽ ሊያገኝ በሚችልበት ሁኔታ በመመሪያዎች ላይ በግልፅ በማስቀመጥ እንዲሁም ንግድ ፈቃድን በተመለከተ ከአዲሱ የንግድ ሚኒስቴር አዋጅ ቁጥር 686/2002 ጋር እንዲስማማ ጥረት ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ የነበረ ሲሆን በተጨማሪም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ኤጀንሲው የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገባ ይገባል፡፡

43. የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡ ኤጀንሲው በላከው የድርጊት መርሃ ግብር ላይ የወጣው የመሬት ሊዝ አዋጅ የህብረት ስራ ማህበራት መሬት ስለሚያገኙበት ሁኔታ በግልጽ ያላስቀመጠ በመሆኑ በወጣው የመሬት አጠቃቀምና የሊዝ አዋጅ መሰረት የህብረት ስራ ማህበራት መሬት የሚያገኙበት ሁኔታ እንዲካተት ወይም በሚወጡ የማስፈጸሚያ መመሪያዎች በግልጽ እንዲቀመጥ እስከ መስከረም 2007 ዓ.ም ድረስ ለከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚ/ር በማቅረብ እንደሚፈጸም፣ የህብረት ስራ ማህበራት በወጣው የንግድ አዋጅ 682/2002 እንደገና መመዝገብ

እንደሌለባቸው በኤጀንሲው በ2004 ዓ.ም በጥናት ላይ የተመሰረተ ማብራሪያ ለንግድ ሚኒስቴር በማቅረብ የጋራ ግንዛቤ የተወሰደ መሆኑና ከዚህም በተጓዳኝ በህብረት ስራ ማህበራት ማደራጃ አዋጅ እና በንግድ ምዝገባ አዋጅ ላይ አሻሚ የሆኑ አንቀፆች እንዲሻሻሉ ስምምነት የተደረሰ በመሆኑ እስከ ሚያዚያ 2007 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ በህብረት ስራ ማህበራት ማደራጃ እና በንግድ ምዝገባ አዋጅ አሻሚ የሆኑ አንቀጾች እንደሚስተካከሉ፣ የህብረት ስራ ማህበራቱን የሚመለከቱ የግብር ዓይነቶች ተፈጻሚ ማድረግ እንዲችሉ በእቅድ እንደተያዘና ከ2006 በጀት ዓመት ጀምሮ የህብረት ስራ ማህበራቱን በሚመለከቱ የግብር ዓይነቶች ግንዛቤ በማሳደግ ተፈጻሚ እንደሚሆን ገልፀዋል፡፡

44. በክትትል ኦዲቱ ወቅት

- የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ የህብረት ስራ ማህበራትን አዋጆችና ደንቦች ተግባራዊ ለማድረግ ኤጀንሲው ካዘጋጃቸው 21 የአፈፃፀም መመሪያዎች ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ህብረት ስራ ኤጀንሲ እና በናሙና በታዩ ክፍለ ከተማ እና ወረዳ ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት 17፣ በእርግብ ህብረት ስራ ዩኒየን 4፣ በየካ ክ/ከ ቀበሌ 11/12/08 ሸማቾች ህብረት ስራ ማህበር 4 መመሪያዎች ፣በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን ህብረት ስራ ኤጀንሲ 8፣ በጉማ ወረዳ ህ/ስ/ኤጀንሲ 8፣ በደ/ምሸዋ ዞን ህ/ስ/ኤጀንሲ18፣ በወንጪ ወረዳ ህ/ስ/ኤጀንሲ 6 የደረሳቸው ሲሆን በጅማ ሁለገብ ህ/ስራ ዩኒየን 7፣ በሊበን ሁለገብ ህ/ስራ ዩኒየን 19፣ በጉዲና ድነግዴ ገ/ቁ/ብ 3 መመሪያዎች፣ ኦሞ በቆ ሁለገብ ህ/ስ/ማህበር እና ኢልቡ ሁለገብ ህ/ስ/ማህበር ምንም መመሪያ ያልደረሳቸውና በመመሪያዎቹ መሰረት ግንዛቤ ያልተሰጣቸው መሆኑ፣
- በአማራ ክልል በናሙና በታዩ በጎዛምን ወረዳ ህብረት ስራ ጽ/ቤት በክልል በኩል የወጡ 8 መመሪዎች ብቻ የደረሰው ሲሆን በባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ በክልሉ በኩል የወጡ መመሪዎች በሶፍት ኮፒ የደረሳቸው ቢሆንም በፌደራልም ሆነ በክልል በኩል ለወጡ መመሪያዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ያልተፈጠረላቸው መሆኑ እንዲሁም የዘንባባ ንብ ውጤቶችና ግብይት ዩኒየን በየጊዜው የህብረት ስራ ማህበራትን አዋጆችና ደንቦች ተግባራዊ ለማድረግ በፌደራልና በክልል የሚወጡ መመሪያዎች እንዲደርሳቸው አለመደረጉ፣

- በደቡብ ክልል 19፣ አዲስ አበባ መስተዳድር 6 ፣ሀረሪ ክልል 8 ፣ ድሬዳዋ መስተዳድር 9 ፣ አማራ ክልል 7 እና ትግራይ ክልል 21 የህብረት ስራ ማህበራት የህብረት ስራ አዋጅና ደንብና አፈፃፀም ለማስፈፀም የወጡ መመሪያዎች ምንም የሌላቸው ሲሆን በአማራ ክልል 1 ፣ በትግራይ ክልል 1 እንዱሁም በደቡብ ክልል 2 ህብረት ስራ ማህበራት በተሟላ መልኩ መመሪያ የሌላቸው መሆኑን በክትትል ኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማሰረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡ ዝርዝሩ **በአባሪ 3** ተያይዟል፡፡
- ድጋፍ በሚሹ ክልሎች ሶማሌ ክልል 52 ፣በአፋር ክልል 25 እና በቤንሻንጉል ክልል 24 ህብረት ስራ ማህበራት የህብረት ስራ ማህበራትን አዋጆችና ደንቦች ተግባራዊ ለማድረግ የተዘጋጁ መመሪያዎች ተደራጅተው አለመኖራቸውን ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ መቻሉ፣
- የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ የክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት እና ህብረት ስራ ማህበራት በመመሪያው መሰረት ስለመስራታቸው በተሟላ መልኩ ክትትልና ድጋፍ አለማድረጉ፣
- በክትትል ኦዲቱ ወቅት ድጋፍ በሚሹ ክልሎች ከሚገኙ ህ/ስራ ማህበራት በአፋር ክልል 31፣ በሱማሌ 43 ፣በጋምቤላ 7 እንዲሁም ደቡብ ክልል 1፣ ትግራይ ክልል 2 እና ሀረሪ ክልል 1 ህ/ስራ ማህበሩ የሚገለገልበት ጽ/ቤት ወይም መስሪያ ቦታ የሌለው መሆኑን ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ መቻሉ፣ (ዝርዝሩ **በአባሪ 6** ተያይዟል፡፡)
- በአዲስ አበባ ክልል በናሙና በታዩ ህብረት ስራ ማህበራት የካ ክ/ከ ቀበሌ 11/12/08 ሸማቾች ህብረት ስራ ማህበር እና እርግብ ህብረት ስራ ዩኒየን ያላቸው መስሪያ ቦታ ጊዜያዊና የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የሌለው መሆኑ፣ በየካ እና በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ስር የሚገኙ ህብረት ስራ ማህበራት ማበረታቻ ላይ ከገቢ ግብር እና ከቦታ ጋር በተያያዘ ችግር እንደሚገጥማቸው የየክፍለ ከተማዎቹ ህብረት ስራ ማስፋፊያ የስራ ኃላፊዎች የገለፁ መሆኑ፣
- በኦሮሚያ ክልል በናሙና በታዩ፡-
    - ኢልቡ የገበሬ ሁለገብ ህ/ስ/ማህበር 1971 ዓ.ም የተመሰረተና በድጋሚ በ1994 ዓ.ም የተመዘገበ ሲሆን የራሱ የሆነ የጽ/ቤትና የመስሪያ ቦታ ቢኖረውም እስካሁን ድረስ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) የሌለው መሆኑ፤ጉዲና ዲነግዴ ገ/ቁ/ብ /ህ/ስ/ማ በ2000 ዓ.ም የተመሰረተ ሲሆን ለማህበሩ ጽ/ቤት መስሪያ ቦታ

በ2004 ዓ.ም የወንጪ ወረዳ አስተዳደርን በድጋሚ በ2009 ዓ.ም ከወረዳ እስከ ዞን መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ድረስ በደብዳቤ ቢጠይቁም ምላሽ አለማግኘታቸውን መግለጻቸው፣

- በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ሊበን የገበሬዎች ሁለገብ ህ/ስራ ዩኒየን በ1997 ዓ.ም የተመሰረተ ሲሆን በአግሮ ፕሮሰሲንግ ስራ ላይ ለመሰማራት መሬት ጠይቆ ባለማግኘቱ ከብር 500,000 በላይ ወጪ በማውጣት ከመንግስት መሬት በሊዝ በመግዛት የእንሰሳት መኖ ማቀነባበሪያ ማሽን በመትከልና ለምረት ማከማቻ መጋዘን የሰራ ሲሆን በተጨማሪም ከአባላቱ የሚሰበስበውን ድንች እሴት በመጨመር ለገበያ ለማቅረብ የድንች አግሮ ፕሮሰሲንግ ማሽን ለመትከል እና ለአርሶ አደሩ የግብርና አገልግሎት መስጪያ ማዕከል ለመክፈት መሬት ጠይቆ ባለማግኘቱ በሊዝ በገዛው ግቢ ውስጥ የድንች አግሮ ፕሮሰሲንግ ማሽኑን ለመትከል የተገደደ ሲሆን ለሁለቱም ፋብሪካ ምርት ማከማቻና ለገበሬዎች አገልግሎት መስጫ ማዕከል ቦታ ባለማግኘቱ ተጨማሪ 207,000.00 ብር የኪራይ ወጪ በማውጣት ከግለሰብ ተከራይቶ እየሰራ መሆኑ፣
- ጅማ ሁለገብ ህ/ስ/ዩኒየን በ1996 ዓ.ም 81 አባል ማህበራትን በማቀፍ የተቋቋመ ሲሆን ወደ አግሮ ፕሮሰሲንግ ለመሸጋገር እንዲሁም የዩኒየኑን የጽ/ቤት ህንጻ የመስሪያ ቦታ/መሬት ጠይቆ ባለማግኘቱ በ2005 ዓ.ም በሊዝ ከመንግስት መሬት በመግዛት ወደ ስራ የገባ መሆኑ፤ጅማ ዞን ጉማ ወረዳ ህብረት ስራ ኤጀንሲ የስራ ኃላፊዎች በተደረገላቸው ቃለ መጠየቅ በሰጡት ምላሽ በወረዳው ከሚገኙት ገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበራት መካከል 47 የገንዘብ ቁጠባና ብድር ማህበር የራሳቸው የሆነ የጽ/ቤት መስሪያ ቦታ የሌላቸው ሲሆኑ የጽ/ቤት መስሪያ ቦታ ጠይቀው ማግኘት ባለመቻላው በጊዜያዊነት በትውስት እየተጠቀሙ እንደሚገኙ የገለፁ መሆኑ፤

- በአማራ ክልል የባህር ዳር ዙሪያው ወረዳ ከመሬት ጋር ተያይዞ በባህር ዳር ከተማ ሰባት ሀሚት፣ህይወት አለም ጤና እና ምስራቅ ጮራ ሁለገብ ህብረት ስራ ማህበር የማህበሩ ይዞታ የነበረውን መሬት የከተማው መዘጋጃ ቤት መውሰዱ እና ክስ ላይ መሆናቸውን እንዲሁም የጎዛምን

ወረዳ ካሉ ገንዘብ ቁጠባና ብድር ህ/ስራ ማህበራት መካከል 5 ህብረት ስራ ማህበራት ለጽ/ቤት አገልግሎት የሚውል ቦታ አለማግኘታቸውን ኃላፊዎቹ መግለፃቸው፣ በናሙና በታየው ዘንባባ የማር ውጤቶችና ግብይት ዩኒየን በስሩ የሚገኘውን የዩኒየኑን ቦታ ሙሉ በሙሉ የማር ማጣሪያ ማሽን በመትከሉና ለጽ/ቤት መስሪያ የሚሆን ትርፍ ቦታ በማጣቱ ዩኒየኑ በተደጋጋሚ የጽ/ቤት መስሪያ ቦታ ቢጠይቅም ባለማግኘቱ ተጨማሪ የኪራይ ወጪ በወር ብር 10,000 በማውጣት ከግለሰብ እንዲከራይ የተገደደ መሆኑ፤

በክትትል ኦዲቱ የታዩ ግኝቶች ናቸው፡፡

45. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በቃለ መጠይቅ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት ምላሽ ኤጀንሲው ለክልል አሰልጣኞች ደንብና መመሪያዎችን እንደሚልኩ እንደ አጠቃላይ በአሰራር ደረጃ እስከ ህብረት ስራ ማህበራት መድረስ እና የደረሰውን መመሪያ ለቀጣይ ፈፃሚ ማስተላለፍ ላይ ክፍተት መኖሩን፣ የህብረት ስራ ማበረታቻን በተመለከተ ከቦታ ጋር በተያያዘ የፌዴራሊዝም ስርዓት እንደመሆኑ ህብረት ስራ ኤጀንሲ እስከ ታች ወርዶ መስራት እንደማይችል ነገር ግን ከአዲስ አበባ፣ አማራ እና ቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል አመራሮች ጋር እየተነጋገሩ መሆኑንና የተወሰኑ መስተካከሎች መኖራቸውን፣ ኦሮሚያና ደቡብ ክልሎች ላይ ግን አሁንም ችግሮች ያሉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም በረቂቅ የክትትል ክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ላይ በሰጡት ምላሽ ችግሮችን በዘላቂነት ሊፈታ በሚያስችል መልኩ የነበረውን አዋጅ በማሻሻል አዲስ በወጣው የህብረት ስራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 ውስጥ የተሻሻለ አንቀጾች እንዲካተቱ የተደረገ ሲሆን ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ለፌደሬሽን ምክር ቤት ቀርቦ በሁሉም ክልሎች ያለምንም ችግር ተግባራዊ እንዲደረግ የምክር ቤቱ ይሁንታ እንዲያገኝ የተደረገ በመሆኑ አዋጁ ተግባራዊ መደረግ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ህብረት ስራ ማህበራት ያለምንም ችግር የድጋፍና ማበረታቻ ተጠቃሚ እንዲሆኑ እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

46. የባለሥልጣኑ ኃላፊች ይህን ይበሉ እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከከለስናቸው መረጃዎችና በመስክ በናሙና ባየናቸው የህብረት ስራ ማህበራት ላይ በፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ የወጡ መመሪያዎችና የተለያዩ ማኑዋሎች በአብዛኛው ለህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት እና ለህብረት ስራ ማህበራት ያልደረሳቸውና በመመሪያው ላይ በቂ ግንዛቤ ያልተሰጠበት እንዲሁም ከመስሪያ ቦታ ጋር በተያያዘ በአዲስ በወጣው

አዋጅ መሰረት ለህብረት ስራ ማህበራተወ በምደባ ማግኘት እንዳለባቸው ያስቀመጠ ቢሆንም ኤጀንሲው አዋጁን ለማስፈጸም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ችግሩን ለመፍታት ያደረገው ጥረት አነስተኛ በመሆኑ በርካታ ህብረት ስራ ማህበራት የመስሪያ ቦታ ችግር ያለባቸውና ጽ/ቤት የሌላቸው ማህበራት በመኖሩ፣ ከመሬት ጋር ተያይዞ ባለው ጉዳይም ችግሩ ያልተቀረፈ በመሆኑ አስተያየቱን አልተቀበልነውም፡፡

47. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ የህብረት ስራ ማህበራትን አዋጆችና ደንቦች ተግባራዊ ለማድረግ ካዘጋጃቸው 21 የአፈፃፀም መመሪያዎችና ማኑዋሎች ለህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት እና ማህበራት በተሟላ መልኩ ባለመድረሳቸው እና ባለመተግበራቸው ማህበራቱ ማግኘት የሚገባቸውን ጥቅም እንዳያገኙ እና በመንግስት የወጣውን የህብረት ስራ ደንብንና ህግን አክብረው እንዳይሰሩ በተጨማሪም በመንግስት ለህብረት ስራ ማህበራት የሰጣቸውን ድጋፎች ተጠቃሚ ባለመሆናቸው ተጨማሪ አላስፈላጊ ወጪ እንዲያወጡ ያደርጋል፡፡

## የህብረት ሥራ ደንብና መመሪያዎች ሲዘጋጁ የሴቶችን ወጣቶች ጉዳይ ያካተቱ መሆናቸውንና ተግባራዊነታቸውን በተመለከተ፣

48. በቀድሞው ኦዲት ወቅት የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ያዘጋጃቸው መመሪያዎች ውስጥ ሴቶችና ወጣቶችን በተሳትፎና በአመራር ሰጭነት በሚያበረታታ መልኩ አለማስቀመጡ፤ በአገራችን በ35 ዓይነት የተሠማሩ ህብረት ስራ ማህበራት ቢኖሩም የፌዴራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ እስከ 2003 ዓ.ም ለ6ቱ ዓይነት የህብረት ስራ ማህበራት የአደረጃጀት መመሪያ ያዘጋጀ ሲሆን ለ29ኙ (83%) አለመዘጋጀቱ፡፡ በናሙና ከታዩ የክልል ኅብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ ኤጀንሲዎች ከ6ቱ የአደረጃጀት መመሪያዎች አብዛኛው ያልተገኙ መሆኑ፤የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ የአማራ፣ የደቡብ፣ የኦሮሚያ፣ የትግራይ፣ የአዲስ አበባና የድሬደዋ ክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች በህብረት ስራ ማህበራት የስራ መመሪያዎች አተገባበር ላይ ክትትል አለማድረጉ ታውቆ ነበር፡፡

49. በዚሁ መሰረት ሴቶችና ወጣቶች በህብረት ስራ ማህበራት ያላቸውን ተሳትፎ ለማበረታታት ቁጥራቸውንና በአመራር ሰጪነት ተሳትፏቸውን ለማሳደግ በሚያስችል መልኩ በመመሪያዎች ውስጥ ሊካተት እና በእያንዳንዱ ዓይነት የኅብረት ሥራ ማህበራት ዘርፍ ወይም ሁሉንም ህብረት ስራ ማህበራት የሚመለከት ወጥ የሆኑ የአደረጃጀት መመሪያዎችን እንዲሁም መመሪያ

ላልተዘጋጀላቸው በማዘጋጀት፣ በማሠራጨት እና ተግባራዊነቱን በመከታተል በየክልሉ የሚገኙ የኅብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ አካላት አዳዲስ አይነት ኅብረት ስራ ማህበራትን እንዲያደራጁ ድጋፍ ሊሰጥ እንዲሁም ማህበራት በደንብ አፈፃፀም መመሪያ መሰረት ስለመሰራታቸውና በስራ ላይ ያጋጠሟቸውን ችግሮች ለመቅረፍ እንዲያስችላቸው ኤጀንሲውና የህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ለችግሮቻቸው የመፍትሔ ሃሳብ በማዘጋጀት በየሩብ ዓመቱ ሊከታተሉ ይገባል የሚል የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ በተጨማሪም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ኤጀንሲው የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገባ ይገባል፡፡

50. የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡ ኤጀንሲው በላከው በድርጊት መርሃ ግብር ላይ የሴቶችን ተጠቃሚነት ፣ተሳትፎ እና አመራር ሰጪነትን ለማረጋገጥ ጥናት የተካሄደ መሆኑን እና 2006 ዓ.ም ጀምሮ በተጠናው ጥናት መሰረት ሴቶችን በተለያዩ ሁኔታ ተጠቃሚ የሚያደርግ መመሪያ በማዘጋጀት ፣ በየክልሎች የስርዓተ ጾታ ጉዳይ የሚከታተልና የሚደግፍ ክፍል በማደራጀት የእያንዳንዱን ስራዎችን ቼክ ሊስት አካል በማድረግ እናም በእያንዳንዱ የህብረት ስራ ማህበራት ዘንድ በዕቅድ እንዲያዝና እንዲሰራ ክትትልና ድጋፍ እንደሚደረግ ገልፀዋል፡፡

51. በክትትል ኦዲቱ ወቅት

- ኤጀንሲው መመሪያዎች ተግባራዊ ስለመሆናቸው በናሙና መርጦ ክትትል ያደረገባቸው ህብረት ስራ ማህበራት መኖራቸው፣ የሴቶችና ወጣቶች አባላት ተሳትፎ እና በአመራር ሰጪነት ዙሪያ ያላቸውን ድርሻ ለማሳደግ የተዘጋጁ መመሪዎች በተመለከተ አዲሱ አዋጅ 985/2009 ዓ.ም ላይ የሴቶችን ተሳትፎ ቢያንስ 30 በመቶ በአመራርነት ደረጃ ማስቀመጥ የሚል መጠቀሱ፣ የስርአተ ፆታን በተመለከተ የተዘጋጀ የስልጠና ማንዋልም መኖሩ፣ በ2006 የስርዓተ ፆታ ኦዲት አድርጓል፡፡

ይሁን እንጂ በክትትል ኦዲቱ ወቅት

- ህብረት ስራ ኤጀንሲ በየክልሉ ያሉ ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላትን እንዲሁም ከክልሎች ጋር በመሆን የህብረት ስራ ማህበራት በተዘጋጁት የደንብ አፈፃፀም መመሪያዎች መሰረት ስለመስራታቸው እና በዚህ ዙሪያ ስላጋጠሟቸው ችግሮች በየሩብ ዓመቱ ክትትል ያላደረጉ መሆኑ፤

- ሴቶች በህብረት ስራ ማህበራት በአባላትም ሆነ አመራር ሰጭነት ተሳትፎዋቸው እንዲያድግ በአዋጅ፣ መመሪያ እና በእቅድ ከማስቀመጥ ውጭ የተጠናከረ ስራ አለመሰራቱ፣
- በደቡብ ክልል 20፣ በሀረሪ ክልል 3፣ ትግራይ ክልል 9 ህብረት ስራ ማህበራት የሴቶች ተሳትፎ በአባልነት አነስተኛ መሆኑን ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት መቻሉ፣ ዝርዝሩ **በአባሪ 1** ተያይዟል፡፡
- በፌደራል ህብረት ስራ አዋጅ 985/2009 ዓ.ም ቁጥራቸው የሚፈቅድ አባል ሴቶች በሚገኙበት ማንኛውም ህብረት ስራ ማህበር ውስጥ ቢያንስ 30 % አመራር በሴት መያዝ እንዳለበት የተቀመጠ ቢሆንም በክትትል ኦዲቱ ወቅት በአዲስ አበባ ከተማ በናሙና በታዩ የካ ክ/ከተማ ህብረት ስራ ማደራጃ ጽ/ቤት፣ ቂርቆስ ክ/ከተማ ጽ/ቤት ማደራጃ፣ ቂርቆስ ክ/ከተማ ስር ወረዳ 01 ህብረት ስራ ማደራጃ ጽ/ቤት ተደራጅተው የሚገኙ የህብረት ስራ ማህበራቱ የሴቶች ተሳትፎ አናሳ መሆኑ እንዲሁም እርግብ ህብረት ስራ ዩኒየን ካለው 10 የአመራር አባላት ውስጥ የሴቶችና ተሳትፎ በአመራርነት ምንም የሌለ እና በየካ ክ/ከ ቀበሌ 11/12/08 ሸማቾች ህብረት ስራ ማህበር ካለው 17 የአመራር አባላት ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ በአመራርነት 4ቱ (23.5%) ብቻ መሆኑ፣
- በኦሮሚያ ክልል በናሙና ከታዩ ጅማ የገበሬዎች ህብረት ስራ ዩኒየን በጠቅላላው ካለው ከ12 ስራ አመራር ኮሚቴዎች ውስጥ የሴቶች በአመራርነት ምንም አለመኖሩ፣ ሊበን ሁለገብ ህ/ስ/ዩኒየን በጠቅላላው ከ12 ስራ አመራር ኮሚቴዎች ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ በአመራርነት 16 %፣ ኢሊቡ ሁለገብ ህ/ስ/ማ በጠቅላላው ከ13 ስራ አመራር ኮሚቴዎች ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ በአመራርነት አለመኖሩ፣፣ጉዲነ ዲነግዴ ገ/ቁ/ብ/ጎ/ስ/ማ በጠቅላላው ከ16 ስራ አመራር ኮሚቴዎች ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ በአመራርነት 25 %፣ ኦሞ በቆ ሁለገብ ህ/ስ/ማ በጠቅላላው ከ13 ስራ አመራር ኮሚቴዎች ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ በአመራርነት ምንም የሌለ መሆኑ፣
- በአማራ ክልል በናሙና በታዩ ባህር ዳር ከተማ እና እና ምስራቅ ጎጃም ዞን ጎዛምን ወረዳ ህብረት ስራ ኤጀንሲ ስር ከሚገኙ ህብረት ስራ ማህበራት ውስጥ ከገንዘብና ቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበራት ውጪ ያሉ ህብረት ስራ ማህበራት ላይ የሴቶች ተሳትፎ እና ሴቶችን ወደ

አመራርነት ማምጣት አነስተኛ ሲሆን በወረዳ ደረጃ ይህንን ችግር ለመቅረፍ የተሰራ ስራ አለመኖሩ እንዲሁም በዘንባባ ንብ ውጤቶችና ግብይት ዩኒየን በጠቅላላው ከ10 ስራ አመራር ኮሚቴዎች ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ በአመራርነት ምንም የሌለ መሆኑ፣

- በአገሪቱ 67 አይነት ዘርፍ ህብረት ስራ ማህበራት ቢኖሩም የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ለ6ቱ ዘርፍ ህብረት ስራ ማህበራት ብቻ የአደረጃጀት መመሪያ ያለው መሆኑ እንዲሁም ወጥ የሆነ የአደረጃጀት መመሪያ የሌለው መሆኑ፤ በአዲስ አበባ በናሙና በታዩ የካ ክ/ከተማ ህብረት ስራ ማደራጃ ለ 2 አይነት ዘርፍ፣ ቂርቆስ ክፍል ከተማ ህብረት ስራ ማደራጃ 3 አይነት ዘርፍ፣ በቂርቆር ክ/ከተማ ወረዳ 01 ህብረት ስራ ማደራጃ 2 አይነት ዘርፍ እንዲሁም በአዲስ አበባ ህብረት ስራ ኤጀንሲ 1(የሸማቾች) አይነት ዘርፍ የአደረጃጀት መመሪያ ብቻ ያላቸው መሆኑ በክትትል ኦዲቱ ወቅት በተከለሱ ማስረጃዎች፣ በቀረቡ መጠይቆች እና በመስክ ምልከታ የተለዩ ግኝቶች ናቸው፡፡

52. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች በቃል መጠይቅ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት ምላሽ መመሪያዎች ስለመተግበራቸው ናሙና ወስደው ክትትል እንደሚያደርጉ፤ ሴቶችን በተመለከተ በኤጀንሲው ሴቶችን የሚደግፍ ክፍል መቋቋሙንና በሁሉም ክፍሎች የሚታቀዱ እቅዶች ሴቶችን ያማከሉ ሆነው እንዲሰሩ እንደሚያደርጉ፣ የስርዓተ ፆታ ኦዲት ማድረጋቸውን እና የስርዓተ ፆታ ማንዋል መኖሩን ፣ አዳማ ላይ በሐምሌ 2009 ዓ.ም ከሴቶችና ወጣቶች ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የንቅናቄ መድረክ ማዘጋጀታቸውን፣ የገ/ቁ/ብ ህብረት ስራ ማህበራት ላይ የሴቶች ተሳትፎ ጥሩ ቢሆንም የሌሎች ዘርፎች ህብረት ስራ ማህበራት ላይ ግን የሴቶች ተሳትፎ በአባልነትም ሆነ በአመራር ደረጃ አናሳ መሆኑን፣ የአደረጃጀት መመሪያዎቹን በተመለከተ ወጥ የሆነ የአደረጃጀት ማንዋል የሌለ መሆኑንና ያሉት 6 አይነት የአደረጃጀት ማንዋሎች ሁሉንም ዘርፍ ያካተቱ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

53. ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ መመሪያዎች በክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ስለመተግበራቸው ክትትል የማይደረግ በመሆኑ እና ያሉት 6 የአደረጃጀት ማንዋሎቹም ለ67 አይነት ህብረት ስራ ማህበራትን ሊያካትቱ አለመቻላቸውን በናሙና ተመርጠው መጠይቅ ከቀረበላቸው ከታዩ የክልል ባለሙዎች ለመረዳት በመቻሉ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል አያስችልም፡፡

54. የህብረት ስራ ማህበራት በተዘጋጁት የደንብ አፈፃፀም መመሪያዎች መሰረት ስለመስራታቸው እና በዚህ ዙሪያ ስላጋጠሟቸው ችግሮች በየሩብ ዓመቱ ክትትል ባለማድረጋቸው ህብረት ስራ ማህበራት ያሉባቸውን ክፍተቶች እና መፍትሄ የሚሹ ችግሮቻቸው ተለይተው እንዳይፈቱ ያደርጋል፡፡ ሴቶች በህብረት ስራ ማህበራት አባላትም ሆነ አመራር ሰጭነት ተሳትፎዋቸው እንዲያድግ የተጠናከረ ስራ ባለመሰራቱ ሴቶች በህብረት ስራ ማህበራት ላይ ያላቸው ተሳትፎ አነስተኛ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ወጥ ወይንም ለእያንዳንዱ ህብረት ስራ ዘርፍ የአደረጃጀት መመሪያ ባለማውጣቱ ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ያለማደራጃ መመሪያ እንዲሰሩ እና አሰራራቸው ወጥ እንዳይሆን እና ክፍተት እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡

**የህብረት ስራ ማህበራት ሂሳብ በየዓመቱ ኦዲት ስለመደረጉ፤**

55. በቀድሞው ኦዲት ወቅት የፌዴራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ በመላ አገሪቱ ለሚገኙ ኅብረት ሥራ ማህበራት አንድ ወጥ የሆነ የሂሣብ ምርመራ /ኦዲት/ ማድረጊያ ጊዜ አለመኖር ፣ በፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲና በሕብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት (በአማራ፣ በአዲስ አበባ፣ በኦሮሚያ እና በደቡብ) ከተደራጁ የህብረት ስራ ማህበራት ውስጥ በአጠቃላይ በአማካይ በ2001 ዓ.ም 80.8%፣ በ2002 ዓ.ም 77.7%፣ በ2003 ዓ.ም 84.2% ኅብረት ሥራ ማህበራት ኦዲት አለመደረጋቸው እና ድጋፍ በሚሹ ክልሎች እስከ 4 አመት ኦዲት ሳይደረጉ የቆዩ ህብረት ስራ ማህበራት ያሉ መሆናቸው ታይቷል፡፡

56. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ የህብረት ስራ ማህበራት ሂሳብ ወቅቱን ጠብቆ እንዲመረመር እና ተአማኒነት ያለው ኦዲት ለማድረግ እንዲያስችል ለህብረት ስራ ማህበራት አንድ ወጥ የሆነ የሂሳብ አያያዝና ምርመራ ስርአት እንዲኖር ሊያደርግ እንደሚገባ እንዲሁም የህብረት ሥራ ማህበራት የትርፍ ክፍፍል እንዲያደርጉና ያሉበትን ደረጃ በማወቅ የበለጠ እንዲሠሩ የፌዴራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲና የክልል ኅብረት ሥራ ማስፋፊያ አካላት ኅብረት ሥራ ማህበራትን በየአመቱ ኦዲት በማድረግ ወይም በተወካይ ኦዲት እንዲደረጉ እገዛ በማድረግ የኦዲት ሽፋንን ማሳደግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ የነበረ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ኤጀንሲው የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገባ ይገባል፡፡

57. የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡ ኤጀንሲው በላከው የድርጊት መርሃ ግብር ላይ የህብረት ስራ ማህበራቱ ሂሳብ መዝጊያ ጊዜ ሰኔ 30 እንዲሆን በፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ በ2004 ዓ.ም ወጥቶ ተግባራዊ በመደረግ ላይ እንደሆነና ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚነቱን እንደሚከታተሉ ፣ ወቅታዊ የኦዲት አገልግሎት የህብረት ስራ ማህበራት ለመስጠት የሚያስችል ከፌደራል እስከ ወረዳ የአደረጃጀት መዋቅር ጥናት በ2006 እንደተዘጋጀና ሁሉም ክልሎች የስራ ሂደት እንዲቀርፁ እንደተደረገ፣ በ2007 ዓ.ም የአደረጃጀት መዋቅሩን ተግባራዊ እንደሚደረግ፣ የህብረት ስራ ኦዲት ጥራትን በማሻሻል ከ2005 ዓ.ም ተግባራዊ በመደረግ ላይ እንደሆነና ተፈጻሚነቱን በመከታተል በአፈጻጸም የሚታዩ ችግሮችን ከ2006 በጀት ዓመት ጀምሮ እንደሚስተካከል እና በተወካይ ኦዲት የሚደረጉ ህብረት ስራ ማህበራት በማሳደግ የሚከናወን እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

58. በክትትል ኦዲት ወቅት፡

- የኦዲት ሽፋንን ከማሳደግ አኳያ በውክልና ለማስመርመር የወጣ መመሪያ መኖሩ ከተከለሱ ማስረጃዎች እንደ ተስተካከሉ ተግባራት የተወሰዱ ሲሆን

ይሁን እንጂ በክትትል ኦዲት ወቅት፡-

- በፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ በ1ኛው እድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (2004-2007 ዓ.ም) ኤጀንሲው በሀገር አቀፍ ደረጃ ለ130,397 ህብረት ስራ ማህበራት የኦዲት ሽፋን ለመስጠት ቢያቅድም በ1ኛው እድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ 48,748 (37.3 %) ህብረት ስራ ማህበራት ብቻ የኦዲት አገልግሎት የሰጠ መሆኑ፣
- ኤጀንሲው በ2ኛው እድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በ2008 በጠቅላላው ከተደራጁ 67,932 የህብረት ስራ ማህበራት ውስጥ የኦዲት ሽፋን 65 % እንዲሁም 2009 ዓ.ም በጠቅላላው ከተደራጁ 78,687 የህብረት ስራ ማህበራት ውስጥ 75 % የኦዲት ሽፋን ለማድረስ በዕቅድ ቢይዝም በ2ኛው እድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በ2008 ዓ.ም የኦዲት ሽፋኑ 20.3 % እንዲሁም በ2009 ዓ.ም የኦዲት ሽፋኑ 10.2 % መሆኑ፣
- የኦዲት ሽፋንን ከማሳደግ አኳያ በፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ በውክልና ለማስመርመር በ2007 ዓ.ም የወጣው መመሪያ በድጋሚ በ2008 ዓ.ም ተሻሽሎ ቢወጣም፡-

- የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ የክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ህብረት ሰራ ማህበራትን በየስንት ጊዜ ሂሳብ ምርመራ እንዳደረጉ የማጣራት ስራ ያልሰራ መሆኑ፣
- የፌዴራል ኀብረት ሥራ ኤጀንሲ በመላ አገሪቱ ለሚገኙ ኀብረት ሥራ ማህበራት አንድ ወጥ የሆነ የሂሣብ ምርመራ /ኦዲት/ ማድረጊያ ጊዜ የዘረጋ ቢሆንም በፌደራል ደረጃ ኦዲት ከተደረጉ ድጋፍ ከሚሹ ክልሎች በአፋር ከ3-9 ዓመት ፣ በሀረሪ ከ3-8 ዓመት፣ በቤንሻንጉል ከ3-8 ዓመት እንዲሁም በአማራ 11 ዓመት ኦዲት ሳይደረጉ የቆዩ ማህበራት መኖራቸው፣ እና በአዲስ አበባ ከተማ በናሙና ከታዩ የካ ክ/ከተማ ህብረት ስራ ማደራጃ፣ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ህብረት ስራ ማደራጃ እና በቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 01 ህብረት ማደራጃ ከ3-12 አመት ውዝፍ ኦዲት የተደረጉ ህብረት ስራ ማህበራት መኖራቸው፣
- የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ በራሱ ኦዲት ባለሙያዎች ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች በሱማሌ ፣አፋር ፣ ቤንሻንጉል ጉምዝ እና ጋምቤላ ክልሎቹ በሚያቀርቡት ጥያቄ እና ኤጀንሲው በራሱ በእቅድ በመያዝ የኦዲት አገልግሎት የሚሰጥ ሲሆን በ 3 ክልልሎች (በሱማሌ ፣አፋር እና ቤንሻንጉል ጉምዝ ) በ2007 ዓ.ም ከተደራጁ 2,947 ህብረት ስራ ማህበራት ውስጥ በኤጀንሲው ባለሙያዎች 12 (0.4%) ፣በ2008 ዓ.ም ከተደራጁ 4,564 ህብረት ስራ ማህበራት ውስጥ 34 (0.74%) ፣በ2009 ዓ.ም ከተደራጁ 4,836 ህብረት ስራ ማህበራት ውስጥ 34 (0.7%) ብቻ ኦዲት ማድረጉን እንዲሁም በጋምቤላ ክልል እስከ 2009 በጀት አመት 2,021 ህብረት ስራ ማህበራት ቢደራጁም በኤጀንሲው ባለሙያዎች ኦዲት ያልተደረገ መሆኑን ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ መቻሉ፣
- ድጋፍ በሚሹ ክልሎች በኤጀንሲው ህብረት ስራ ማስፋፊያ ዳይሬክቶሬት ውስጥ ህብረት ስራ ማህበራቱን ለማጠናከር ከተያዙት ህብረት ስራ ማህበራት ሶማሌ ክልል በ2008 በጀት አመት 35 ህብረት ስራ ማህበራት በ2009 በጀት አመት 17 ህብረት ስራ ማህበራት ፣በአፋር ክልል በ2008 በጀት አመት 25 ህብረት ስራ ማህበራት፣ በቤንሻንጉል ክልል በ2008 በጀት አመት 23 ህብረት ስራ ማህበራት ውስጥ አብዛኞቹ ኦዲት ተደርገው የማያውቁ መሆኑ፣ (ዝርዝሩ **በአባሪ** 4 እና 5 ተያይዟል፡፡)
- በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን በቁጥር ምገ/10/10.11/2 በቀን 22/7/2007 ዓ.ም በላከው ደብዳቤ የአባልነት ወንበር በመግዛት በአባልነት ከተመዘገቡ 32 መሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራት፣ ዩኒየኖች እና ፌደሬሽን መካከል ኤጀንሲው ለማህበራቱ

ቅድሚያ በመስጠት ኦዲት ባለማድረጉ ወይንም ማህበራቱ በራሳቸው በባለስልጣኑ በተመዘገቡ ገለልተኛ ኦዲት ድርጅቶች የማህበራቱ ኦዲት እንዲያስደርጉ አማራጭ ያልተሰጣቸው በመሆኑ በ2006 ዓ.ም በአባልነት ከተመዘገቡት ውስጥ 4 ህብረት ስራ ማህበር ብቻ የኦዲት ሪፓርት ያቀረቡ በመሆኑና ሌሎች ባለማቅረባቸው የስራ እንቅፋት በመፍጠሩ ለሌሎች ገለልተኛ የኦዲት ድርጅቶች ኦዲት እንዲያስደርጉ አማራጭ እንዲሰጣቸው ለኤጀንሲው የገለጸ ሲሆን በድጋሚ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን በቁጥር ምገ/10/10.3/21 በቀን 20/7/2009 ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤ የምርት ገበያ አባል የሆኑ ህ/ስ/ማህበር አባል በመሆን የሚጠበቅባቸውን ግዴታዎች ከመወጣት አኳያ በየዓመቱ ኦዲት ማስደረግና የኦዲት ሪፓርት ማቅረብ ሲሆን የምርት ገበያ አባል ማህበራቱ በየዓመቱ በኤጀንሲው ኦዲት የማይደረጉ በመሆኑ እና ህብረት ስራ ማህበራትን በውክልና ለማስመርመር የተሸሻለው መመሪያ በ2008 ዓ.ም የወጣ ቢሆንም ተግባራዊ ባለመሆኑ በአሰራር ላይ ክፍተት መፍጠሩን ለፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ በተጻፈ ደብዳቤ ያሳወቀ መሆኑን ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት መቻሉ፣

በክትትል ኦዲቱ ወቅት በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች የተወሰዱ ግኝቶች ናቸው፡፡

59. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በቃለ መጠይቅ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ኦዲትን በተመለከተ የባለሙያ እጥረትና ፍልሰት በመኖሩ ክፍተቶች መኖራቸው በቀጣይ አቅም ያላቸው ህብረት ስራ ማህበራት በራሳቸው ኦዲት እንዲያስደርጉ በማድረግ፣ የህብረት ስራ ማህበራት ኦዲት ማህበር በማቋቋም እና የሰው ሃይሉን ፍልሰት ለመቀነስ እንዲቻል የደሞዝ ስኬሉን በማሻሻል ለመስራት ማሰባቸውን እና በውክልና ኦዲት በተመለከተ የማስመርመር አቅጣጫውን ያስቀመጡ ቢሆንም ተግባራዊነቱ ላይ ክትትል አለማድረጋቸውን ገልፀዋል፡፡

60. የህብረት ስራ ማህበራት ወቅቱን የጠበቀ ሂሳብ ምርመራ ባለማድረጋቸው ወቅቱን ጠብቀው የትርፍ ክፍፍል እንዳያካሂዱ፣ ጠቅላላ ጉባዔ እንዳይጠሩ፣ የብድር አገልግሎት እንዳያገኙ እንዲሁም የማህበሩ ገንዘብም ለተቀደለት አለማ መዋልና ለመዋሉን ችግሮች ካለም በወቅቱ እንዳይፈታና ያሉባቸውም ክፍተቶች ተለይተው እንዳይታረሙ ያደርጋል፡፡

**ኤጀንሲውና የሕብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት የሚሰሩትን የኦዲት ሪፖርት በጠቅላላ ጉባኤ ስለመጽደቁና በሪፖርቱ መሰረት እርምጃ መወሰዱን በተመለከተ፣**

61. በቀድሞው ኦዲት ወቅት የፌዴራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ በራሱ ባለሙያዎች የሰራውን የኦዲት ሪፖርት ለሕብረት ስራ ማህበራት ጠቅላላ ጉባኤ አቅርቦ አለማፀደቁ፣ በኦዲት ሪፖርት የተሰጡ አስተያየቶችን ተግባራዊነትም አለመከታተሉ እና ኤጀንሲው ኦዲት ላደረጋቸው የኅብረት ሥራ ማህበራት በኦዲቱ መሠረት ያሉበትን ደረጃ የሚያሣይ ሠርተፊኬት አለመስጠቱ የተገኙ ግኝቶች ነበሩ፡፡

62. የፌዴራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ እና የክልል ኅብረት ሥራ ማስፋፊያ አካላት የሚሰሩትን የኦዲት ሪፖርት ለኅብረት ሥራ ማህበራት ጠቅላላ ጉባዔ አቅርበው ሊያስፀድቁና በሪፖርቱ የተሰጡ አስተያየቶችን ተግባራዊነት ሊከታተሉ እንደሚገባ፣ የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲና የክልል ኅብረት ሥራ ማስፋፊያ አካላት በሂሣብ ምርመራ ወቅት አስቀድሞ በተቀመጡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ደረጃ መስጫ መመዘኛ ነጥቦች መሠረት ለኅብረት ሥራ ማህበራት የሚገኙበትን ደረጃ የሚያሣይ ሠርተፊኬት በመስጠት ኅብረት ሥራ ማህበራት የውድድር መንፈስ እንዲፈጥሩ፣ ተጨማሪ አባላትን ማፍራት እንዲችሉ እንዲሁም ከአበዳሪ አካላት ጋር የበለጠ ተጠናክረው እንዲሠሩ ሊያደርጉ ይገባል የሚል የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ የነበረ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ኤጀንሲው የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልኩ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገባ ይገባል፡፡

63. የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡ ኤጀንሲው በላከው የድርጊት መርሃ ግብር ላይ በ2001 እና በ2003 በተዘጋጀው የስራ ሂደት ጥናቶች መሰረት የኦዲት ስራው የሚያልቀው ለጠቅላላ ጉባኤ ከቀረበ በኃላ በመሆኑ የመለየት ስራ እንደተሰራና ለክልሎች ግብረ መልስ እንደተሰጠ፣ ከ2007 ጀምሮ በተጠናከረ ሁኔታ ተግባራዊ እንደሚደረግና የየህብረት ስራ ኦዲተሮችም ይህንን መፈጸም እንዲችሉ ግንዛቤ የማሳደግና ክትትል የማድረግ ሥራ እንደሚሰራ ፣በ2005 እና በ2006 ዓ.ም ጠንካራና ደካማ ህብረት ስራ ማህበራትን መለየት የሚያስችል የህብረት ስራ ማህበራት ብቃት ማረጋገጫ መመሪያ የተዘጋጀና መመሪያው በተግባር የተፈተሸ በመሆኑ በ2007 ዓ.ም የብቃት ማረጋገጫ የሚሰጥ መዋቅር በማደራጀት ሁሉም ክልሎች ተግባራዊ እንደሚያደርግ ገልፀዋል፡፡

64. በክትትል ኦዲቱ ወቅት

- ሁለት ኦዲት ሪፖርቶች ላይ ማለትም የአዲስ አበባ ቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ዩኒየን ኃላ/የተ(2009 ዓ.ም ላይ የ7 አመት ውዝፍ ኦዲት

የተሰራ) እና የግብርና ሚኒስቴር የገንዘብና ብድር የህብረት ስራ ማህበር (2009 ዓ.ም ላይ የ3 አመት ውዝፍ ኦዲት የተሰራ) የኦዲት ሪፖርቹ ለጠቅላላ ጉባኤ መቅረባቸውን የሚያሳይ ማስረጃዎች በኤጀንሲው መያያዛቸው ፣ በአገር ደረጃ የህብረት ስራ ማህበራትን ደህንነት ለማስጠበቅና በማህበራት ላይ የሚታዩ ጉድለቶችን ተከታትሎ ለማስመለስና ከፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ እስከ ወረዳ ድረስ የህግ ባለሙያ መዋቅር የዘረጋ መሆኑ እንዲሁም የብቃት ደረጃ ምስክር ወረቀት ለመሰጠት በፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ውስጥ የብቃት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት በ2007 ዓ.ም በመዋቅሩ እንዲካተት መደረጉ የተሸሻሉ ተግባራት ሲሆኑ፣

ይሁን እንጂ በክትትል ኦዲት ወቅት፡-

- በናሙና ከታዩት በአዲስ አበባ ከተማ የካ ክ/ከ ቀበሌ 11/12/08 ሸማቾች ህብረት ስራ ማህበር የመዝናኛዎቹ ክበብ ፣ እርግብ ህብረት ስራ ዩኒየን ፣ በጅማ ዞን በጎማ ወረዳ የሚገኘው የኢልቡ ሁለገብ ህብረት ስራ ማህበር ፣ በሀረር ክልል ሀረር ቢራ ሰራተኞች ገ/ቁ/ብ እና ቬራ ፓስታ ሰራተኞች ገ/ቁ/ብ፣ በአማራ ክልል የዘንባባ ንብ ውጤቶችና ግብይት ዩኒየን ፣መረዋ ሀደሬ ሁለገብ ህ/ስ/ማ፣ ሰጋዲ ሁለገብ ህ/ስ/ማ፤ በሱማሌ ክልል አል አሚን የቁም እንሰሳ ግብይት፣ ነጃህ የቁም እንሰሳ ግብይት፣ ነገድ፣ተወከል የቁም እንሰሳ ግብይት ህብረት ስራ ማህበር፤ በአፋር ክልል የፍቅርና ሰላም ፈረስ ጋሪዎች ሁለገብ ህ/ስ/ ማህበር ኦዲት ከተደረጉ በኃላ የኦዲት ሪፓርቱ ለየህብረት ስራ ማህበሮቹ ጠቅላላ ጉባኤ ያልቀረበ መሆኑን ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ መቻሉ፣
- በፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ስር በሚሰሩ ኦዲት ሪፖርቶች ግኝቶች መሰረት ህብረት ስራ ማህበራት ክፍተቶቻቸውን ስለማረማቸው ክትትል አለመደረጉ እና የክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት በሰሩት የኦዲት ሪፖርት መሰረት ህብረት ስራ ማህበራት ስለማስተካከላቸው ክትትል ያደርጉ እንደሆነ የሚያረጋግጥበት ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፤ በአዲስ አበባ ከተማ በናሙና ከታዩ አዲስ አበባ ህብረት ስራ ኤጀንሲ በጉድለት ግኝቶች ላይ እንጂ በሌሎች ግኝቶች ላይ ክትትል የማያደርጉ መሆኑ እንዲሁም የቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 01 ማደራጃ ፤በኦሮሚያ ክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ ኤጀንሲ እንዲሁም በናሙና በታዩ በጅማ ዞን ህብረት

ስራ ኤጀንሲ እና በደ/ም/ሸዋ ዞን ህብረት ስራ ኤጀንሲ በኦዲት ግኝቶች ላይ ስለመስተካከላቸው ክትትል የማያደርጉ መሆኑ፤

- በህብረት ስራ ማህበራት ኦዲት ሪፖርት መሰረት እስከ 2008 ዓ.ም ድረስ ከ5 ክልሎች እና ከ2 ከተማ መስተዳደሮች ብር 722,074,141 የገንዘብ ጉድለት የተገኘ ቢሆንም እስከ 2009 በጀት አመት ማስመለስ የተቻለው ብር 71,225,392.80 (9.8%) ብቻ መሆኑን በክትትል ኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ መቻሉ፤
- የብቃት ደረጃ ምስክር ወረቀት በተመለከተ የብቃት ደረጃ ምስክር ወረቀት ለመስጠት መዋቅር ያላቸው ኦሮሚያ ፣ደቡብና ትግራይ ክልሎች ብቻ ሲሆኑ ከኦሮሚያ እና ደቡብ ክልሎች በስተቀር ሌሎቹ ክልሎች ወደ ተግባር ያልገቡ መሆኑ ፣ በክልል ደረጃ ለተሰጠው ሰርተፍኬት ክልሎች ሪፖርት ከመላክ ውጪ የሰጡትን ሰርተፍኬት መረጃ የማይያዝ እና የህብረት ስራ ማህበራት በሚያገኙት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ውጤት ላይ በመመርኮዝ የሚገኙት ማበረታቻዎች እንዳሉ የህብረት ስራ ማህበራት የብቃት ደረጃ ማረጋገጫ መመሪያ(2007 ዓ.ም) ላይ የተጠቀሰ ቢሆንም ተግባራዊ አለመደረጉ በክትትል ኦዲቱ የተለዩ ግኝቶች ናቸው፡፡

65. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት ምላሽ ሁሉም የኦዲት ሪፖርቶች ለህብረት ስራ ማህበራት ጠቅላላ ጉባኤ መፅደቃቸውን በተመለከተ መዘግየት ቢኖርም ቀርበው የሚፀድቁ መሆኑን፣ የኦዲት ግኝቶች ላይ ስለመስተካከላቸው እና ከድሮ ጀምሮ ተያይዘው የመጡ ጉድለቶች የሚመለሱበት ሁኔታ ላይ ክፍተቶች መኖራቸውን፤ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬትን በተመለከተ አዲስ አሰራር እንደመሆኑ ለክልሎች ስልጠና የሰጡ ቢሆንም ከተቀመጠለት ጊዜ አንፃር አፈፃፀሙ ላይ ውስንነቶች የሚታዩ መሆኑን ወደፊት በተጠናከረ መልኩ የሚሰሩበት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

66. የኦዲት ሪፖርቶች ለህብረት ስራ ማህበራት ጠቅላላ ጉባኤ ባለመቅረባቸው አባላት ማህበራቸው ላይ ያለውን ክፍተት እንዳያውቁ ብሎም አመኔታ እንዲያጡ የሚያደርግ ሲሆን በኦዲት ግኝቶቹ ላይ ማህበራቱ ያለባቸውን ክፍተቶች ስለማስተካከላቸው በፌደራል እና በክልል ህብረት ስራ ኤጀንሲዎች ክትትል ባለመደረጉ ግኝቶቹ እንዳይታረሙ እንዲሁም ማህበራቱ ለኪሳራ እንዲዳረጉ ያደርጋል፡፡ የህብረት ስራ ማህበራት ብቃታቸው ተመዝነው የሚያገኙት የብቃት

ማረጋገጫ ሰርተፍኬት በሁሉም ክልሎች በተጠናከረ መልኩ እየተሰራ ባለመሆኑ የነብረት ሥራ ማህበራት የውድድር መንፈስ እንዳይኖራቸው፣ ያሉበትን ደረጃ እንዳያሻሽሉ፣ ከአበዳሪ አካላት ጋር የበለጠ ተጠናክረው እንዳይሰሩ እንዲሁም በደረጃቸው መሠረት አዳዲስ አባላትን ማፍራት እንዳይችሉ ያደርጋቸዋል፡፡

**የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲና የክልል ማስፋፊያ አካላት ለተደራጁ ማህበራት የኢንስፔክሽን አገልግሎት መስጠታቸውን በተመለከተ፣**

67. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲና የክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ለተደራጁት ሕብረት ስራ ማህበራት በዓመት አንድ ጊዜ በመደበኛነት የኢንስፔክሽን አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑን፣ በፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ እና በክልል ሕብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት (በአማራ፣ በአዲስ አበባ፣ በኦሮሚያ፣ በቤኒሻንጉል እና በደቡብ) የተደራጁ ህብረት ስራ ማህበራት በአጠቃላይ በ2001 ዓ.ም 71.4%፣ በ2002 ዓ.ም 60%፣ በ2003 ዓ.ም 72.5% በአደረጃጀታቸው፣ በስራ አመራራቸው፣ በስራ አፈፃፀማቸው ወ.ዘ.ተ. የኢንስፔክሽን አገልግሎት አለማግኘታቸው የታዩ ግኝቶች ነበሩ፡፡

68. ኤጀንሲውና የሕብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት የህብረት ስራ ማህበራትን ጠንካራ እና ደካማ ጎን በማወቅ ድጋፍ ለመስጠት እንዲሁም በመመሪያ መሰረት እየሰሩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የኢንስፔክሽን ማንዋል በማዘጋጀት የተደራጁ ሕብረት ስራ ማህበራትን በአደረጃጀታቸው፣ በስራ አመራራቸው፣ በስራ አፈፃፀማቸው ወ.ዘ.ተ. ኢንስፔክት አድርገው የኢንስፔክሽን ግብረ-መልስ ሊሰጧቸው እና በማሻሻያው ሃሳብ መሰረት ስለመስራታቸው ሊከታተሉ ይገባል የሚል የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ የነበረ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ኤጀንሲው የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገባ ይገባል፡፡

69. የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡ ኤጀንሲው በላከው የድርጊት መርሃ ግብር ላይ በ2001 ዓ.ም ህብረት ስራ እንስፔክሽን መመሪያ በፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ተዘጋጅቶ ከ2003-2005 ዓ.ም ተከታታይ የሆነ የማስተዋወቅ ስራ በክልሎች የተሰራ በመሆኑ በ2007 ዓ.ም ጀምሮ በተጠናከረ ሁኔታ የኤንስፔክሽን ተግባሩን ተፈጻሚ በማድረግ ህብረት ስራ ማህበራቱ የህብረት ስራን ህግን አክብረው እንዲሰሩ እንደሚደረግ ገልፀዋል፡፡

70. ይሁን እንጂ በክትትል ኦዲቱ ወቅት ፡-

- በ1ኛው እድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (2004- 2007 ዓ.ም) ኤጀንሲው በሀገር አቀፍ ደረጃ 143,871 ህብረት ስራ ማህበራትን የኢንስፔክን ሽፋን ለመስጠት ቢያቅድም 72,566 (50.4%) ብቻ ኢንስፔክት ያደረገ መሆኑ፣
- በ2ኛው እድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ላይ የህብረት ስራ ማህበራት በአገር አቀፍ ደረጃ የኢንስፔክን ሽፋን በ2008 በጀት አመት 75 % እንዲሁም 2009 በጀት አመት 80 % የኢንስፔክን ሽፋን ለመድረስ ኤጀንሲው በዕቅድ ቢይዝም በ2008 ዓ.ም የኢንስፔክን ሽፋኑ 34.5 % እንዲሁም በ2009 ዓ.ም የኢንስፔክን ሽፋኑ 14.8% መሆኑን በክትትል ኦዲቱ ወቅት ከተከለሰው ማስረጃ ለማወቅ መቻሉ፣
- ኤጀንሲው በራሱ ኢንስፔክሽን ባለሙያዎች ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች በሱማሌ ፣አፋር፣ ቤንሻንጉል ጉምዝ እና ጋምቤላ ክልሎቹ በሚያቀርቡት ጥያቄ እና ኤጀንሲው በራሱ በእቅድ በመያዝ ኢንስፔክሽን አገልግሎት የሚሰጥ ሲሆን በ4 ክልልሎች በ2007 ዓ.ም ከተደራጁ 3,463 ህብረት ስራ ማህበራት ውስጥ በኤጀንሲው ባለሙያዎች 44 (1.2%)፣ በ2008 ዓ.ም ከተደራጁ 5,262 ህብረት ስራ ማህበራት ውስጥ 16 (0.3%)፣ በ2009 ዓ.ም ከተደራጁ 5,643 ህብረት ስራ ማህበራት ውስጥ 28 (0.4%) ብቻ የኢንስፔክሽን አገልግሎት የሰጠ መሆኑ፤
- በኦሮሚያ ክልል በናሙና በታዩ በጅማ ዞን ኢልቡ ሁለገብ ህብረት ስራ ማህበር እና ኦሞ በቆ ሁለገብ ህብረት ስራ ማህበር ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ኢንስፔክት ተደርጎ የማያውቁ መሆኑ፣ኢልቡ ሁለገብ ህብረት ስራ ዩኒን በ2007 ዓ.ም በክልል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ኢንስፔክት የተደረገ ቢሆንም የኢንስፔክሽን ሪፓርቱ ያልተላከላቸው መሆኑ፣
- በአማራ ክልል በናሙና በታየ የዘንባባ ንብ ውጤቶችና ግብይት ዩኒየን በየዓመቱ በክልሉ ህብረት ስራ ኤጀንሲ ኢንስፔክት ቢደረግም ኢንስፔክት ከተደረገ በኃላ በኢንስፔክሽን ሪፓርት መሰረት ስለመስተካከላቸው የኤጀንሲው ባለሙያዎች ክትትል የማያደርጉ መሆኑ፣
